አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ 81ኛ ዓመት ቁጥር 310 ሐምሌ 10 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

«ሕዝባችንን ከችግር ለማውጣት መቻቻልና መደማመጥ አለብን»

- ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ

- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 5 ሺህ 58 ተማሪዎች አስመረቀ

ፎቶ፡- ፀሐይ ንጉሤ

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- አገር በለውጥ ጉዳና እንድትጓዝ በማድረግ ሕዝባችንን ከችግር ለማውጣት መቻቻል፣ መነጋገርና መደማመጥ አለብን ሲሉ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ አስታወቁ።

የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ትናንት በተካሄደው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ምረቃ ሥነ ሥርዓት ላይ ተገኝተው እንደገለጹት፣ ተመራቂ ተማሪዎች ማሕበራዊ፣ አካዳሚያዊና ፖለቲካዊ ፈተናዎችን አልፋችሁ ዩኒቨርሲቲ የገባችሁበትን ዓላማ ማሳካት በመቻላችሁ እንኳን ደስ አላችሁ። አገራችን በልማት፣ በመልካም አስተዳደር፣ በዴሞክራሲ፣ በፍትህና በሰላም ጎዳና እንድትጓዝ ለማድረግ የሁላችንንም ርብርብ ይጠይቃል፤ በተለይ በእውቀት የታነጸ ወጣት ኃላፊነቱ ጉልህ ነው ብለዋል።

አገር በለውጥ ጎዳና እንድትጓዝ በማድረግ ሕዝባችንን ከችግር ለማውጣት መቻቻል፣ መነጋገርና መደማመጥ አለብን ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ የተማረ ሰው የአገሩን ችግር እንዴት እንደሚፈታ ይመራመራል፤ በችግር ውስጥ ያሉትን የወገኖችን ስቃይ ይረዳል። ከችግር ለማውጣት እንደሚተጋ ገልጸዋል።

ተመራቂዎች በተመረቃችሁበት የትምህርት ዘርፍ ወደ ተግባር በመቀየር ለቤተሰብና፤ ለወገንና ለአገር አገልጋይ መሆን እንደሚጠበቅባቸው ገልጸው፤ መማር

«ሕዝባችንን ከችግር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ

ዶክተር ለገሰ ቱሉ

ሕግን በማስከበርና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ኢትዮጵያን የማበልጸግ ስራ እየተሰራ መሆኑ ተገለጸ

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- በአንድ በኩል ሕግን እያስከበርን በሌላ በኩል ምርትና ምርታማነትን እያሳደግን ኢትዮጵያን የሚያበልጽግ ስራ እያከናወን ነው ሲሉ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዶክተር ለገሰ ቱሉ ገለጹ። የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ሰራተኞችና ተጠሪ ተቋማት በኦሮሚያ ክልል ምእራብ አርሲ ዞን ችግኝ ተክለዋል።

ሕግን በማስከበርና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ኢትዮጵያ፣ ኤርትራና ሶማሊያ የጀመሩትን ትብብር አጠናክረው የራሳቸውን ችግር በራሳቸው ሊፈቱ እንደሚገባ ተጠቆመ

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ፣ ኤርትራ እና ሶማሊያ ትብብር ለምዕራባዊያን ሥጋት የሚሆነው ፍላጎታቸውን እንደልብ እንዲፈጽሙ ስለማያደርግ ሀገራቱ ትብብራቸውን በማጠናከር የራሳቸውን ችግር በራሳቸው ሊፈቱ እንደሚገባ የፖለቲካ ተንታኝ የሆኑት ኤፍሬም ማዴቦ ገለጹ።

የፖለቲካ ተንታኙ ኤፍሬም ማዴቦ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደገለጹት፤ ትልቅ የሕዝብ ቁጥርና የቆዳ ስፋት ያላት ኢትዮጵያ እና ሥትራቴጂክ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ያላቸው ኤርትራ እና ሶማሊያ በተለያዩ ዘርፎች የሚያደርጉት ትብብር ማደግ ምዕራባዊያንን ያሠጋል። የቀንዱ ሀገራት ትብብር ለምዕራባዊያን ሥጋት የሚሆነው ፍላጎታቸውን በቀጠናው ውስጥ እንደልብ እንዲፈጽሙ ስለማያደርግ ነው ያሉት አቶ ኤፍሬም፤ ሆኖም ሀገራቱ ትብብራቸውን በማጠናከር የራሳቸውን ችግር በራሳቸው ሊፈቱ ይገባል ብለዋል።

ሦስቱ ሀገራት እ.ኤ.አ በሴፕቴምበር 2018 በቀጠናው ሰላምና መረጋጋት ያላቸውን ትብብር ለማጠናከር እና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ለማፋጠን ያለመ ስምምነት ተፈራርመዋል። ሀገራቱ በትብብር ስምምነታቸው መሰረት ሽብርተኝነትን፣ ሕገወጥ ስደትን፣ ሕገወጥ ዕፅ ዝውውርን እና የጦር መሣሪያ ዝውውርን የመሳሰሉ በጋራ የሚገጥሟቸውን ሥጋቶች በጋራ ለመታገል የጋራ ዕቅድ ነድፈዋል።

የፖለቲካ ተንታኙ አቶ ኤፍሬም ግን የተፈረሙት ስምምነቶች ሽብርተኝነትን በጋራ ከመከላከል እና ሕገወጥ ስደትን፣ የሕገወጥ ዕፅ እና የጦር መሣሪያ ዝውውርን ከመከላከል ባሻገር አንድምታ እንዳላቸው ይናገራሉ።

ምዕራባዊያኑም ከነዚህ ሀገራት የትብብር ማደግ ጋር በተያያዘ ሥጋት ውስጥ የሚገቡት እጃቸውን በቀጠናዊ ሁኔታዎች ውስጥ እያስገቡ የብጥብጥ ቀጠና ማድረግ ስለማይቻላቸው መሆኑን ያነሳሉ።

«ኢትዮጵያ፣ ኤርትራና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ኤፍሬም ማዴቦ

መምህር ፍሬዘር ጥላሁን

ድጋፉ ለመልሶ ግንባታ እና ለኢኮኖሚው መነቃቃት ትልቅ ፋይዳ አለው

ገጽ 4

ከደረሰኝና ሕግ ማስከበር ጋር የተያያዙ ችግሮች አሁንም የገቢ አሰባሰቡ ተግዳሮት መሆናቸው ተነገረ

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- ከደረሰኝና ሕግ ማስከበር ጋር ተያይዞ ያሉ ችግሮች አሁንም ተግዳሮት ሆነው የቀጠሉና ቢሮው በቀጣይ ለመፍታት በትኩረት የያዛቸው ጉዳዮች መሆናቸውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ሃላፊ አቶ ሙሉጌታ ተፈራ በተለይ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለጹት፤ በበጀት አመቱ ቢሮው የሥነምግባር ጉድለት ባሳዩ 200 በሚደርሱ ባለሙያዎች ላይ እርምጃ የወሰደ ሲሆን ቁጥራቸው 855 የሚሆኑ ያለደረሰኝ ግብይት ሲፈጽሙ የነበሩ አካላትን በመያዝ ለሚመለከተው የፖሊስ አካል ሰጥቷል።

ከደረሰኝና ከሕግ ማስከበር ጋር ተያይዞ ያሉ ችግሮች አሁንም ተግዳሮት ሆነው የቀጠሉ በመሆናቸው መፈታት አለባቸው ያሉት አቶ ሙሉጌታ፤ አሁንም ድረስ ግብር ከፋዩ ስለታክስ፣ ሕጎችና ደንቦች ተገንዝቦ ከመስራት አንጻር ክፍተቶች አሉ ብለዋል። ለዚህም የግብር ከፋዩን ግንዛቤ በማሳደግ ሙብቱና ግዴታውን አውቆ እንዲሰራ ማድረግ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

እንደ አቶ ሙሉጌታ ገለጻ፤ ቢሮው ከጊዜ ወደ ጊዜ የማስፈጸም አቅሙ እየጨመረ መጥቷል። በተደረጉ የማሻሻያ ስራዎች በተቋሙ ባለው የሰው ኃይል ከተጠናው አኳያ 54 በመቶ አካባቢ ነው። ይህም በአማካይ አንድ ሰው የሁለት ሰው ስራ እየሰራ ውጤቱን ማምጣት ተችሏል። ከዚህ በፊት ከነበረበት ሁኔታም አፈጻጸሙ

አቶ ሙሉጌታ ተፈራ

እንዲሻሻል ሆኗል። ይህ ማለት ግን ከሚፈለገው ደረጃ ላይ ደርሷል ማለት አይደለም። በቀጣይም በሰው ኃይልና በቴክኖሎጂ የማጠናከር ስራ በትኩረት ይሰራበታል ብለዋል።

የታክስ መሰረቱንም አሁን ካለበት ለማስፋት እቅድ ተይዟል ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ የሚነግዱ ነገር ግን ንግድ ፈቃድ የሌላቸው ግብር የማይከፍሉ ነጋዴዎችን መለየትና ወደ ንግድ ሥርዓቱ እንዲገቡ በእቅድ ተይዞ ከንግድ ቢሮ ጋር በጋራ እየተሰራ እንደሆነ ጠቁመዋል።

አቶ ሙሉጌታ እንዳሉት፤ በባለሙያዎች የተፈጸሙ የሥነምግባር ጥሰቶችን በመለየት ለማስተካከል ጥረት ተደርጓል። ከእርምጃው በፊት ባለሙያዎችን ማስተማር፤ ግብር ከፋዩ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው በማድረግና በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ በማይገባ አካል ደግሞ ሕጋዊ እርምጃ ይወሰዳል። በዚህ አግባብ 200 የሚደርሱ ባለሙያዎች ላይ ከቀላል እስ ስራ ማሰናበት የደረሰ እርምጃ ተወስዷል።

በዚህ አመት ቁጥራቸው 855 የሚሆኑ ያለደረሰኝ ግብይት ሲፈጽሙ የነበሩ አካላትን በመያዝ ለሚመለከተው የፖሊስ አካል አስተላልፏል ያሉት አቶ ሙሉጌታ፤ ጥፋት በሚፈጸሙበት ጊዜ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን አደራጅቶ ለሚመለከተው የፖሊስ አካል የማስረከብና ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ የማድረግ ስራ ተሰርቷል ሲሉም ተናግረዋል።

አሁንም የአገልግሎት አሰጣጡ እድገት ያሳየ ቢሆንም ከተገልጋዩ ብዛትና ከሚሰጠው የአገልግሎት ብዛት አኳያ ገና ብዙ መስራት ይጠበቅብናል ብለዋል።

ከሕግ ማስከበር አኳያ አሁንም ለአገልግሎትና ዕቃ በደረሰኝ መሸጥ ባንድ በኩል በሻጩና የደረሰኝ አለመቁረጥ ችግር፣ በገዥው በኩል ደረሰኝ ተቀብሎ አለመግዛት ያልተሻገርናቸው ችግሮች ናቸው ያሉት አቶ ሙሉጌታ ችግሮቹ በመሰረታዊነት እንዲፈቱ መስራት እንደሚጠይቅና በቀጣይም የስራ ዘመን የትኩረት አቅጣጫዎች ሆነው ይቀጥላሉ ብለዋል።

ግብር ከፋዮችም ከመንግሥት አሰራር ውጪ የሆነ ጉዳይ ሲገጥማቸው በ7075 ነጻ የስልክ መስመር በመደወል መረጃ ማግኘትና መስጠት ይችላሉ ተብሏል።

«ችግኞችን የምንተክለውና ሥራዎችን የምንሠራው ኢትዮጵያን እያሰብን ከሆነ ለሀገር ግንባታ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል»

- አቶ ጌትነት ታደሰ
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈፃሚ

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- ችግኞችን የምንተክለውና ሥራዎችን የምንሠራው ስለኢትዮጵያ እያሰብን ከሆነ ሀገር ለመገንባት ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል ሲሉ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጌትነት ታደሰ ገለጹ። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አመራርና ሠራተኞች በትናንትናው ዕለት በእንጦጦ ፓርክ ችግኝ ተክለዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጌትነት ታደሰ ትናንት በእንጦጦ ፓርክ በተካሄደው በችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ላይ እንደገለጹት፤ ችግኞችን የምንተክለውና ሥራዎችን የምንሠራው ስለኢትዮጵያ እያሰብን ከሆነ ሀገር ለመገንባት ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል። የኢትዮጵያን ሁለተናዊ ብልጽግናም ያፋጥናል።

ዛሬ የተከልናቸው ችግኞች ከተንከባከብነው ነገ አድገው አድገው ዛፎች ይሆናሉ፤ ይህ ደግሞ ለልጅ ልጆች የሚተርፍ ሥራ ነው። አቶ ጌትነት አሁን ወቅቱ የአረንጓዴ አሻራ የምናሳርፍበት ስለሆነ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ስለኢትዮጵያ መድረክን ሲያዘጋጅ የአረንጓዴ አሻራን ከተቋሙ ተግባራት ጋር አጣምሮ እየሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት "አረንጓዴ አሻራ ስለኢትዮጵያ" በሚል መርሐ ግብር ጅማ ላይ ከቀናት በፊት ችግኝ ተከላ መጀመሩን የገለጹት አቶ ጌትነት፤ አረንጓዴ አሻራን የተቋሙ አንድ ተግባር አድርጎ በመሥራት ላይ እንደሚገኝ እና ይህም ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን ገልጸዋል።

በጅማ ከተማ በተካሄደው በስድስተኛው የስለኢትዮጵያ መድረክ ዝግጅት ላይ አረንጓዴ አሻራ የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናት ጭምር በተገኙበት መካሄዱን አውስተው፤ ለወደፊቱ በሚካሄዱ ስድስት የስለኢትዮጵያ ዝግጅቶች ላይም የአረንጓዴ አሻራ ፕሮግራም እንደሚካሄድ ጠቁመዋል።

ዋና ሥራ አሥፈፃሚው፤ ችግኞችን መትከል ብቻ

ፎቶ፡- ከማኅበራዊ ገጽ

ሳይሆን እንክብካቢዎችን ሳይለያቸው እናሳድጋቸዋለን በማለትም በሠራተኞች እና በተቋሙ ሥም ቃል ገብተዋል።

የመርሐግብሩ አስተባባሪ እና በድርጅቱ የሥርዓተ ፆታ ጽሕፈት ቤት ተጠባባቂ የሆኑት ወይዘሮ ብርሃኔ ደመቀ በበኩላቸው፤ በድርጅቱ ሰራተኞች ባለፈው ዓመት የተተከሉ ችግኞች 80 በመቶ መጽደቃቸው በባለሙያዎች እንደተረጋገጠ ተናግረዋል።

በየሦስት ወሩ ለችግኞች እንክብካቤ እንድናደርግ ቃል ገብተናል ያሉት ወይዘሮ ብርሃኔ፤ በዘንድሮው ዓመት ልዩ ፕሮግራም ተቀርፆ የችግኞች እንክብካቤ እንደሚካሄድ ጠቁመዋል።

ስለ አረንጓዴ አሻራ ጥቅም ሁሉም ሰው ገብቶታል ብዬ አስባለሁ ያለችው ከየተቋሙ ሠራተኞች መካከል አንዷ ጋዜጠኛ መልካምሥራ አፈወርቅ፤ አሁን ክፍተቶች የሚታዩት በችግኝ ተከላ ላይ ሳይሆን በእንክብካቤ ላይ ነው ብላለች።

ችግኝ ተክሎ ሳይንከባከቡ መቅረት ወልዶ እንደመጣል የሚቆጠር እንደሆነም ተናግራለች። የተተከሉ ችግኞች እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል፤ በየጊዜው ልንንከባከባቸው ይገባል ስትል ገልፃለች።

ሌላው የችግኝ ተከላው ተሳታፊ ጋዜጠኛ ዳርጌ ካሕሳይ ዘንድሮ ለአራተኛ ጊዜ በመርሐ ግብሩ መሳተፉን ገልጿል። ማሕበረሰቡ ችግኝ ተከላ ላይ በቂ ግንዛቤ ይዟል ብዬ አምናለሁ ያለው የኢትዮጵያን ሄራልድ ጋዜጠኛ ዳርጌ፤ በእንክብካቤ ላይ ያሉ ችግሮችን በመቅረፍ የአረንጓዴ አሻራን የበለጠ ውጤታማ ማድረግ ይቻላል ብዬ አምናለሁ ብሏል።

የጉለሌ ክፍለ ከተማ የተተከሉ 800 ችኞችን ስፖንሰር ማድረጉ ታውቋል።



አቶ መላኩ አለበል

ከሥነምህዳሩ ጋር የሚስማማ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለመገንባት የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ወሳኝ መሆኑ ተገለጸ

ገመቺ ከድር

አዲስ አበባ፡- የኢንዱስትሪ ዘርፉን ከሥነምህዳር ጋር የተስማማ በማድረግ ሠላሟ የተጠበቀና በኢኮኖሚ የበለጸገች ሀገር ለመገንባት የዜጎች አረንጓዴ ልማትን የማረጋገጥ ሥራ ወሳኝ መሆኑን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ።

ሚኒስቴሩ የሚጠበቅበት የዜግነት አገልግሎት እየተወጣ መሆኑን ገልጿል። ሚኒስቴሩ "አሻራችን ለትውልዳችን -ለትውልድ እንስራ ፤ ለኢትዮጵያ እንትከል" በሚል መሪ ቃል በሃዲያ ዞን ሾኔ ከተማ የአረንጓዴ አሻራ መርሃግብር አካሂዷል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል በፕሮግራሙ ላይ እንደገለጹት፤ ሚኒስቴሩ በሀገር ግንባታ ሂደት በሚደረገው የአረንጓዴ አሻራ ልማትና በዜግነት አገልግሎት ላይ እየተሳተፈ ይገኛል።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሾኔ ከተማ ተገኝቶ አረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ማካሄዱ መንግሥት ለአጀንዳው ትልቅ ትኩረት መስጠቱን ያሳያል። የአከባቢው ሕብረተሰብም በአረንጓዴ አሻራን በማኖር አካባቢውን በመቀየርና በመንከባከብ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበክት ጥሪ አቅርበዋል።

በክረምት በጎ አድራጎት ሥራም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ትውልድ ለመገንባት የሚያስችል የዓይነትና የገንዘብ ድጋፍ ማድረጉን ገልጸዋል።

ለማሕበራዊ አገልግሎት የሚውል የተለያዩ የትምህርት መማሪያ መሣሪያዎች ሦስት ሺ ደብተርና ሰባት ሺህ እስክብሪቶን ጨምሮ የተለያዩ የጽህፈት መሣሪያዎችን ማበርከቱን ገልጸዋል።

የመማሪያ ክፍል እጥረትን ለመፍታት ለትምህርት ቤት ግንባታ የሚውል አንድ ሚሊዮን ብር እንደሚያበረክቱ ቃል ገብተዋል።

ትምህርት ቤቶች በመልካም ሥነምግባር የታነጹ ዜጎች መፍለቂያ በመሆናቸው በቀጣይም የመማር ማስተማር ሂደቱ ምቹ እንዲሆን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድጋፉን እንደሚቀጥል ገልጸው፤ ሕብረተሰቡም ልጆቹን በማስተማርና የተተከሉ ችግኞች በመንከባከብ ሃላፊነቱን እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል።

የሀዲያ ዞን አስተዳዳሪ አቶ አብርሃም መጫ በበኩላቸው በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተግባራዊ የተደረገው መርሐ ግብር የሚያስመሰግን ነው። ችግኙ የአካባቢውን ሥነ ምህዳር በማስጠበቅ ፤ ጉልህ ሚና አለው ያሉት አቶ አብርሃም፤ ለተደረገው ድጋፍ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን አመስግነዋል። ሕብረተሰቡ የተተከሉ ችግኞች እንዲከባከብም አሳስበዋል።

ርዕሰ አንቀፅ

ህመማችንን እንወቅ፤ ስፈውሱም እንደማመጥ!

ሀገር እንደ ሀገር የምትታመምበትና ከፍ ያለ ዋጋ የምትከፍልበት የታሪክ ምእራፍ አለ። የዚያች ሀገር ሕዝቦች በሽታውን ፈጥነው ማወቅ ከቻሉና ለመፍትሄው መረባረብ የሚያስችል መደማመጥ ከፈጠሩ በህመሙ ምክንያት ሊፈጠር የሚችለውን ሀገራዊ ጥፋት ማስቆም፤ አልፎም ከሄደ ትርጉም ባለው መልኩ መቀነስ ይቻላል።

በዚህ ታሪካዊ እውነታ ውስጥ ያላለፈ ሀገርና ሕዝብ የለም ለዚህም የአሜሪካው የርስ በርስ ጦርነት፤ በአውሮፓ ሀገራት የተለያዩ ስም እየተሰጣቸው የተካሄዱ የእርስ በእርስ ጦርነቶች፤ በአፍሪካ ሀገራት እስከዛሬ እልባት ያላገኙ የርስ በርስ ጦርነቶችን ማንሳት ይቻላል። አንዳንዶቹ ህመማቸውን አውቀው ፈውስ አግኝተዋል፤ አንዳንዶች ደግሞ ለህመማቸው እስከዛሬ ባይተዋር በመሆናቸው ዋጋ እየከፈሉ አሉ።

በእርግጥ ከየጦርነቶቹ በስተጀርባ ያሉ ምክንያቶች የቱንም ያህል ልዩነት ያላቸው ቢመስሉም ሰው ሰራሽ ስለመሆናቸው ብዙም አነጋጋሪ አይደለም። እነዚህም ከፍ ካለ ራስ ወዳድነት ፣ ዘረኝነት ፣ አክራሪነትና ጽንፈኝነት የሚመነጨና በሁለንተናዊ መልኩ ለዚህ ሰብአዊ እድፍ የተገዙ ናቸው።

ይህ በሽታ በየዘመኑ ሀገራትንና ሕዝቦችን ከፍ ያለ ዋጋ አስከፍሏል። ከአንደኛውና ሁለተኛው ጦርነት በስተጀርባ አለ። ድንገትም በቀጣይ ዘመናትም ዋጋ ማስከፈሉን ስለማቆሙ ማስተማመኛ ሊገኝለት የሚችል አይደለም። ዓለም ከሰብአዊ እሴቶች እየራቀ በሄደ መጠን በሽታው ሊያስከፍል የሚችለው ዋጋ ለግምት ሊከብድ እንደሚችልም ይታመናል።

ሀገራችን ኢትዮጵያም እንደ ሀገር የዚህ ህመም ሰለባ መሆን ከጀመረች ውሎ አድሯል። ህመሙ ዛሬ ላይ ከፍ ያለ አቅም ገዝቶ የዕለት ተዕለት ሕይወታችንን እየተፈታተነ ይገኛል። ከዛሬም አልፎ በነገ ትውልዶች ጤናማ ሕይወት ላይ ሊያስከትል የሚችለው አደጋም ከፍተኛ እንደሚሆን ይታመናል። የነገ ታሪካችን ጥቁር ነጥብ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል።

ገደብ ያጣ ራስ ወዳድነት ፣ ዘረኝነት ፣ አክራሪነትና ጽንፈኝነት የፖለቲካ ማእቀፍ ሆኖ በሀገሪቱ የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ ደቀመዝሙር ማፍራት ከተጀመረ ከሁለት አስርት በላይ ተቆጥሯል። በነዚህ ጊዜያት ውስጥ የተዘራው ዘር ፍሬ አፍርቶ ሀገርን እንደ ሀገር ህመምተኛ ካደረገ፤ የህመሙም አደጋ ስጋት ብሄራዊ ስጋት ከሆነም ሰንብቷል።

በአንድ በከሉል መላው ሕዝብ ህመሙን እንደ ህመም በአግባቡ መረዳት አለመቻሉ፤ ከዚያም በላይ እንደ ሀገር ለህመሙ መድሃኒተኛ የሙብዛቱና እውነታ ችግሩን ውስብስብ፤ ትክለክለኛውን መድሃኒት በአግባቡ ለመውሰድና ሀገራዊ ፈውሱን ለማፍጠን የሚደረገውን ጥረት ፈታኝ አድርጎታል።

ህመሙ ቀን በቆጠረ ቁጥር መልኩን እየቀያየረ ጤናማ ሀገር ለመመስረት የተጀመረውን ለውጥ አደጋ ውስጥ ከትቶታል፤ ለውጡ ያልተገባ ዋጋ እንዲከፍል ከማድረግ ባለፈም መላው ሕዝባችን በለውጡ ያለውን ተስፋ በመሸርሸር ወደ ቀደመው አሮጌው የታሪክ ምእራፍ እንዲመለስ እየጎተተው ይገኛል።

ይህ በሕዝባችን የዘመናት ተስፋ ላይ ተግዳሮት ሆኖ የመጣ የአስተሳሰብ በሽታ ሊያደርስ የሚችለውን ሀገራዊ ጥፋት ለመታደግ ከሁሉም በላይ የህመሙን ምንነት ማወቅ ወሳኝ ነው። ህመሙ የአእምሮ ችግር ያለባቸው ግለሰቦችና ቡድኖችን የሚያጠቃና በሀገር ጉዳይ የሚዘናጉ ዜጎችን በቀላሉ ሊያጠቃ የሚችል ነው።

ዋነኛ መተላለፊያ መንገዱ ስለ አንተ እኔ አውቅልሀለሁ የሚል፤ ብሶትንና ብሶትን መሰረት ያደረገና በዚሁ የሚገራ ትርክትን መሰረት ያደረገ ነው። ሁሌም ሕዝብን የበሽታው ሰለባ በማድረግ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት የሚደረግ ዘመን ያለፈበት የህመምተኛ አእምሮ አመለካከት ውጤትም ነው።

ህመሙ በጊዜ መፍትሄ ካላገኘና እየሰፋ ከሄደ የሀገርን ህልውና የቱን ያህል እንደሚፈታተን ከሶሪያ፣ ከሊቢያና ከየመን አሁነኛ እውነታ መማር ይቻላል። ሀገርን አፍርሶ ሕዝብን አስከፊ ችግር ውስጥ ከመክተት ባለፈ ከፍ ያለ ታሪክ ባለቤት የሆኑ ሕዝቦችን ሀገር አልባ ማድረግ የሚያስችል እርግማን ጭምር ነው። ይህንን በሽታ በጊዜ አውቆ መፍትሄ አለማፈላለግ ከጸጸት ባለፈ ለትውልዶች አንገት የሚያስደፋ ታሪክ አስቀምጦ የማለፍ ያህል ነው።

ለበሽታው ፈውስ የማፈላለጉም ሀገራዊ ጥረት በመደማመመጥ ላይ የተመሰረተና በህመሙ ላይ ትኩረት ያደረገ ሊሆን ይገባል። የመድሃኒተኞች መብዛት በራሱ ለህመሙ ዕድሜ ሊሰጠው እንደሚችልና የአመለካከት ልዩነቶች መድሃኒት በመፈለግ ሂደቱ ተግዳሮት ሊሆኑ እንደማይገባ ማስተዋል ተገቢ ነው። የአመለካከት ልዩነቶች የሚስተናገዱትና ፍሬ የሚያፈሩት በጤናማ ሀገር ውስጥ መሆኑን ማሰብም መልካም ነው!

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ሳፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

ከሃይማኖቶች አስተምህሮ ያስወጣ ያልሰለጠነ ፖለቲከኛነት

ሚሳት ኢያሱ

ያልሰለጠነ ፖለቲካ በበሃሪው የእኔ...የእኔ ማለትን ስለሚወድ በሀሳብ ልእልና ሳይሆን በጉልበት አሸንፎ መውጣትን፤ በሴራ ጠልፎ የመጣልን መንገድ ይከተላል። ፖለቲከኞች መተዳደሪያቸው ሕገእግዚአብሄር ሳይሆን ሕገመንግሥት ነው። በመሆኑም ላይተዳደሩበት ሕግ ያረቅቃሉ፣ ሕግያሻሽላሉ፣ መልሰው ራሳቸው ያወጡትን ሕግያፈርሳሉ። ጥቂት የማይባሉ ፖለቲከኞችን እንደታዘብናቸው ትኩረታቸውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ አድርገው ግላዊ ፍላጎታቸውን ያስቀድማሉ።

የስልጣኔ ቁንጮ ተብላ በምትጠራው አሜሪካ ውስጥ የሚኖሩ ፖለቲከኞች በንግግራቸው መጨረሻ «God bless America» እግዚአብሄር አሜሪካን ይባርክ ይላሉ። ፖለቲካው በቅጡ ባልሰለጠነባቸው ሀገራት የሚኖሩ ፖለቲከኞች ግን ምድራዊውን እንጂ ሰማያዊውን ዓለም ብዙም ስለማይናፍቁት ይመስላል ለሞራልና ለሃይማኖታዊ እሴቶች ግድ የላቸውም፤ ለህሊና ዳኝነትም አይገዙም። አንዳንዶቹ እንደውም የትጥቅ ትግል ውስጥ ገብተው በሰበበ ፖለቲካ መለኮታዊ ሕግጋትን እየጣሱ ያልታጠቁና ጉዳዩ የማይመለከታቸው ንጹኃን ወንድሞቻቸውን ይጨፈጭፋሉ።

ሃይማኖት መተዳደሪያው ሕገ- እግዚብሄር ስለሆነ ፍቅርን፣ መቻቻልን፣ አንድነትን፣ መደጋገፍንና መተዛዘንን ይሰብካል። አንዱ ለተቸገረ ወንድሙ እንዲደርስ ያስተምራል። ሕገ- እግዚአብሄር፤ ሰዎች ይቅርባይ፣ እርቅን ተቀባይና ሰላም ወዳድ እንዲሆኑ ይፈልጋል። ግድያን፣ጥላቻን፣ ዘረኝነትን፣ ወገንተኝነትን፣ በዳይነትንና ግፍአድርጊነትን ያወግዛል።

አንድ የፖለቲካ ቡድን የሚከተለው አስተሳሰብ ለሀገርና ለሕዝብ የሚበጅ ይሁንም አይሁንም፤ በአንድ ሀገር የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ የእርሱ ሀሳብ ብቻ ገኖ እንዲታይ ይፈልጋል።በተለይም ተቀራርቦ የመነጋገርና የዲሞክራሲ ባህል ባልዳበረባቸው ሀገራት እንዲህ አይነቱን ችግር መመልከት የተለመደ ነው።

በሊቢያ፣ በየመንና ሶሪያ የተከሰቱት የእርስ በርስ ጦርነቶች መነሻቸው ብዙ ውጪያዊ ጉዳይ ቢኖረውም እስካሁን መፍትሄ ማግኘት ያልቻለው የእኔ ፖለቲካዊ መስመር ትክክል ነው፤ የእናንተ የተሳሳተ ነው ከሚል አስተሳሰብ የመነጨ መሆኑ አንድ ማሳያ ነው።

ተቀራርቦ በመነጋገር ሀሳቦችን ማስታረቅ እየተቻለ የአንድ ሀገር ዜጎች በሁለትና ሶስት ጎራ እየተከፋፈሉ አላስፈላጊ ጦርነት በማድረግ ለበርካታ ንጽኃን ዜጎቻቸው እልቂትና ለኢኮኖሚ ድቀት ምክንያት ሲሆኑ መመልከት ከፉኛ ያስቆጫል። ማስቆጨት ብቻ ሳይሆን ሰው ሆነን የመፈጠራችንንና ከፍጡራን ሁሉ ተለይቶ የተሰጠንን የማሰብ ጸጋ እንድንጠራጠር ጭምር ያደርጋል።

ይህ ብቻ አይደለም፤ በየትኛውም ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ውስጥ ያሉና መለኮታዊ ትዕዛዝ አድርገን የተቀበልናቸውን አትግደል፣ ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ፣ እናትና አባትህን አክብር ወዘተ የሚሉትን ሃይማኖታዊ እሴቶች ሸርሸሮብናል፤ አርክሶብናልም።

በሰበበ ፖለቲካ ፈጣሪ የማይወደው ሥራ በሰው ልጆች ላይ ሲፈጸም እያየን፤ ያለነው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው ወይስ ሌላ ሀገር? እስከማለት ደርሰናል። በሰው ሀገር ሲፈጸሙ እየሰማን ስንገረምባቸውና ስናዝንባቸው የነበሩ የጭካኔ ተግባራት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገራችን ተደጋግመው ሲከሰቱ እያየ ግራ ያልተጋባ ኢትዮጵያዊ አለ ማለት አይቻልም።

አሸባሪው የህወሓት ቡድን ስልጣን መልቀቁን ተከትሎ ባለፉት አራት ዓመታት የኢትዮጵያን ህዝብ የእርስ በእርስ ጦርነት ውስጥ ለማስገባት ያልፈነቀለው ድንጋይ አለመኖሩ ይታወቃል። በጥቂቶች የግል ፍላጎትና በፖለቲካ አሻጥር ምክንያት በዚህ አራት ዓመት ውስጥ ከፖለቲካ ጋር ምንም አይነት ንክኪ ሳይኖራቸው ያለምንም ጥፋታቸው የተጨፈጨፉትን ንጽኃን ዜጎች ቤቱ ይቁጥራቸው።

ቡድኑ አንዳንዴ በቀጥታ አንዳንዴም በእጅ አዙር ከሰሜን እስከ ደቡብ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ግፍ የፈጸመባቸውና ያስፈጸመባቸውን፣ የገደላቸውና ያስገደላቸውን ዘርዝረን አንጨርሳቸውም።

በኢትዮጵያ ላይ የተለያየ ጥቅምና ፍላጎት ባላቸው የውጭ ሃይሎች እየተደገፈና እንዳለውም ከሲኦል መልዕክተኞቹ ጋር እየተባበር የሰውልጅ በሰው ልጅ ላይ ይፈጽማቸውል ተብለው የማይገመቱ ኢሰብዓዊ ድርጊቶችን ፈፅሟል፤ አስፈጽሟል።

በተለይም ከአሸባሪው ሽኔ ጋር በጋራ እንደሚሠሩ በይፋ ካወጁ በኋላ በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች እሳት እየጫሩ ህጻናት፣ ሴቶችና አረጋውያንን ጨፍጭፈዋል። በቅርቡ በወለጋ ማንነታቸውን መሰረት አድርጎ በዜጎቻችን ላይ የተፈጸመው ጭፍጨፋ ምናልባት በአገራችን ታሪክ ፋሺስት ጣሊያን አብርሃም ደቦጭና ሞገስ አስግዶም ያደረሱበትን ጥቃት ተከትሎ በአዲስ አበባ ከተማና በደብር ሊባኖስ ገዳም የፈፀመውን ጭፍጨፋ የሚያስታውስ ነው።

ሰላማዊ ትግል እንዲያደርግ ጥሪ ተደርጎለት ከነ ሙሉ ትጥቁ ወደ ሀገር ቤት የገባው የኦነግ ሠራዊት መቀሌ ላይ ከአሸባሪው የሕወሓት ቡድን ከፍተኛ አመራሮች ጋር ለውጡን ለማደናቀፍ ተማምሎ ከመጣ ጊዜ ጀምሮ ለራሱ «ሽኔ» የሚል አዲስ መጠሪያ በመስጠት ማንነትን መሰረት ያደረጉና ለጅሮ የሚሰቀጥጡ፤ ለአይን የሚዘገንኑ ጭፍጨፋዎችን በንጹኃን ዜጎች ላይ አካሒዷል። ይህ ሁሉ ግፍና ሰቆቃ የግለኝነት፣ የጥቅመኝነት፣ የዘረኝነት፣ የጨለምተኝነት ወዘተ አስተሳሰቦች መገለጫ ቢሆንም ሰበቡ ፖለቲካ ነው።

አሸባሪው ሕወሓት ሞቼለታለሁ የሚለውንና ብዙኃኑ ድምጽ ሳይሰጥበት ያጸደቀውን ሕገመንገሥት ሳይቀር እየሻረ ባህላዊና ሃይማኖታዊ እሴቶቻችን የማይፈቅዱትን ግፍ በሰው ልጆች ላይ ፈጽሟል። የእርሱ ደቀ መዝሙር የሆነው ሽኔም ተልእኮ እየተቀበለ በሚሠራው ሰይጣናዊ ሥራ «ከመምህሩ ደቀ መዝሙሩ» አስብሎናል።

ኢትዮጵያ ባሳለፈቻቸው ሶስት ሺ ዓመታት በሕገ መንግሥት መተዳደር የጀመረችባቸው ዓመታት ቢታሰቡ ጥቂት ናቸው።አባቶቻችን ሕገመንግስት ጽፈው መተዳደሪያ ደንብ ከማወጃቸው በፊት በሕገ ልቦና እና በሕገ እግዚአብሄር የቀረጹት ተውልድ ቅን፣ ሩህሩህ ስርቆትን፣ ግፍንና በደልን የሚጠየፍ ኢትዮጵያዊ ማንነትን የተላበሰ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በየትኛውም ሃይማኖት ጥላ ስር ይኑር ዛሬም ድረስ ፈሪሃ እግዚአብሄር ያለውና ሕገመንግሥት ባይኖረውም በሕገ እግዚአብሄርና በሕግልቦና ስሪቱ ብቻ መኖር የሚችል ነው። ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ሊፈጸሙ ይቅርና ይፈጸማሉ ተብለው ሊታሰቡ የማይገባቸው የጭካኔ ተግባራት ተፈጽመው ሲታይ ከየት ተነስተን ወደየት እየሄድን ነው የሚል ስጋት ፈጥሮብናል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኢትዮጵያ ውስጥ ፖለቲካን ምክንያት አድርጎ እየተፈጸመ ያለው ኢሰብዓዊ ድርጊት እጃችንን አፋችን ላይ ያስጫነን አሳፋሪ ተግባር መሆኑ ብቻ ሳይሆን በዓለም ማህበረሰብ ዘንድ የነበርንን ክብርና ስም ያነደፈና ያዋረደንም ጭምር ነው።

ሰው የሚያስብ ፍጡር እንደመሆኑ ከየትኛውም ሕግ በላይ ተገዢነቱ ለህሊናው መሆን አለበት። ሆድ ምግብ እንደሚያስፈልገው ሁሉ ለጤናማ ሰውም መልካም ሥራን መሥራት የህሊና እርካታ ይሰጠዋል። ማዘን፣ መርዳት፣ መተባበር፣ መደገፍ ከሰው ልጆች ልብ የሚፈልቁ ቅን አስተሳሰቦች ናቸው። እነዚህ በተፈጥሮ የተጎናጸፍናቸው ጸጋዎቻችን ሕገመንግሥትን ከማክበር በላይ ሰው የመሆናችንን ምስጢር የምንገልጽባቸው ተፈጥሯዊ ባህሪዎቻችን ናቸው።

መጥፎ ነገርን የማንሠራው ሕግን በመፍራት ብቻ ሳይሆን ተፈጥሯችን ስለማይፈቅድልን ነው። ሕገልቦና አንቀጽና ቁጥርን ሳይጠቅስ በሠራነው መጥፎ ሥራ ሰው መሆናችንን እስከምንጠላ ድረስ በህሊና ጸጸት ይቀጣናል። እኛ ኢትዮጵያውያን ከከፋት የራቀ የልቦና ወቅር ስላለን በመጥፎ ድርጊታችን ምክንያት የሚሰማንን የጸጸት ስሜት መሸከም የሚያቅተን ለዚህ ነው። በእርግጠኝነት ሰውን የገደሉ ሰዎች የአዕምሮ ሰላም አያገኙም፤ ዘመናቸውን ሁሉ በጸጸት አለንጋ እየተገረፉ ይኖራሉ። ከዚህ ምድር ሲያልፉም ሰማያዊውን ጸጋ እንወርሳለን የሚል ተስፋ አያደርጉም።

ሰው ከሕገልቦናው ቢያፈነግጥ እንኳ ሰማያዊ ፍርድን በመፍራት ወይም የጽድቅ አክሊልን ለመቀዳጀት በማሰብ ሕገእግዚአብሄርን ወይም ሕገፈጣሪን ያከብራል፤ ለዚህም ፈጣሪ ለሰው ልጅ የሰጣቸውን መተዳደሪያ ደንቦች በተግባር ሊኖራቸው ይጥራል። ግፈኞች፣ ጨካኞችና ፈሪሃ እግዚአብሄር በውስጣቸው የሌላቸው ሰዎች ግን ከሰው ጋር ብቻ ሳይሆን ከፈጣሪያቸውም ጋር የተጣሉ ናቸው።

እያንዳንዱ ሃይማኖት የየራሱ አስተምህሮ አለው። ነገር ግን ፈጣሪ በታላቅ ጥበብ የፈጠረውን የሰው ልጅ «መግደል» ሀጽያት መሆኑን ሁሉም ሃይማኖቶች ይስማሙበታል። ንጽኃንን ካልጨፈጨፉ ትግል ያደረጉ የማይመስላቸው ታጣቂዎች ሕገመንግሥትን ሳይሆን ሕገእግዚአብሄርን የሚፈራ ልብ እና አስተዋይ ህሊና ስላልተሰጣቸው የሰውን ነፍስ ለማጥፋት ይሽቀዳደማሉ። እንደ ሃይማኖታችን አስተምህሮ ፍርድ ይጠብቃቸዋል። ወየውላቸው ለነፍሰ ገዳዮች።

ድጋፉ ለመልሶ ግንባታ እና ለኢኮኖሚው መነቃቃት ትልቅ ፋይዳ አለው

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- ከዓለም ባንክና ሌሎች ዕርዳታ ሰጪ አካላት የተገኘውን ድጋፍና ብድር በአግባቡ መጠቀም ከተቻለ በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸውን አካባቢዎች መልሶ ለማልማት ፤ ኢኮኖሚውን ለማነቃቃትና የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት አወንታዊ አስተዋፅኦ እንደሚኖራቸው ተጠቆመ።

በሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህር ፍሬዘር ጥላሁን ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደገለጹት፤ ከዓለም ባንክ እና ከተለያዩ ዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች የተገኙ ዕርዳታዎች፣ ብድሮችና ድጋፎችን በአግባቡ መጠቀም ከተቻለ ኢኮኖሚውን ከማነቃቃትና የውጭ ምንዛሬ ከማግኘት አንፃር አወንታዊ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል።

መምህር ፍሬዘር የተገኙ ዕርዳታዎች ዒላማ በጦርነት ለተጎዱ እና መፈናቀል ላይ ያሉ የሕብረተሰብ ክፍሎችን መደገፍ እንደሆነ አንስተው፤ ዕርዳታዎቹ የመጨረሻው ዕርዳታ ተቀባይ ድረስ ወርዶ መደገፍ በሚችል ሥርዓት መታገዝ እንደሚገባቸው ጠቁመዋል።

አተገባበሩ ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል ያሉት መምህር ፍሬዘር፤ ዕርዳታዎቹ በአግባቡ ለሚገባው ማሕበረሰብ ከተላለፉ የተገኘው ገንዘብ ኢኮኖሚውን ከማነቃቃትና የውጭ ምንዛሬ ከማግኘት አንፃር እንደ አንድ ተጨማሪ ሀብት የሚወሰድ ነው ብለዋል።

በኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት በጦርነቱ የተጎዱ እና የውስጥ መፈናቀሎች መኖራቸው ይህንን ማቆምና ወደነበረበት ሰላማዊ ሁኔታ መመለስ አስፈላጊ መሆኑን በመጠቆም ተገቢ ድጋፍ ሊያገኙ የሚገባቸው እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው የማሕበረሰብ አካላትም በአግባቡ መለየትና ሕይወታቸውን በተጨባጭ ሊቀይር በሚችል መልኩ ሊቀርብላቸው ይገባልም ሲሉ አክለዋል።

በጦርነቱ በተጎዱ አካባቢዎች ላይ የደረሱ ኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊ ቀውሶች ትምህርት ቤቶች፣ ጤና ተቋማት፤ የውሃ አገልግሎቶች እና መሰል የማሕበረሰብ አገልግሎት መስጫዎች ስለተቋረጡ የተደረጉ ድጋፎች ለእነዚህ መሰረታዊ ፍላጎቶች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ተገቢነት ላለውና ለታለመለት ዓላማ ሊውል ይገባዋልም ብለዋል።

የታዳጊ ሀገራት አብዛኛው መሰረታዊ ፍላጎቶች የሚሟሉት ከአደጉ ሀገሮች በሚሰጥ ድጋፍ፣ እርዳታ እና ብድር በሚገኙ ገንዘቦች መሆኑንና ኢትዮጵያም የዚህ ተጠቃሚ ሆና እንደቆየች የገለጹት የኢኮኖሚ መምህሩ፤ ሆኖም የዕርዳታ ድርጅቶች ሁሉ የራሳቸው ዓላማ ስለሚኖራቸው ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ አሳስበዋል።

መምህሩ የተገኘው ዕርዳታ ሉዓላዊነት ባከበረ መልኩ የሕዝቦችን ፍላጎት አፋጣኝ ምላሽ ከመስጠት አንፃር የሚበረታታ የዲፕሎማቲክ እንቅስቃሴ ውጤት ቢሆንም በዕርዳታ ሰበብ የሚጫኑ ችግሮች እንዳይኖሩ በተጠና ሁኔታ ማከናወን እንደሚገባ ጠቁመዋል።

እንደ መምህር ፍሬዘር ገለፃ፤ በጦርነቱ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል። የተፈናቀሉትም በርካታ ናቸው። ለነዚህ ባስቸኳይ መድረስ ስለሚገባ መንግሥት በዕርዳታና ድጋፍ መጠየቁ አግባብ ነው። ለዚህም ሲባል ያሳያቸው ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴዎች የሚበረታቱ ናቸው። እዚህ ላይ ግን በአፅንዖት ልናየው የሚገባን እንደዚህ ዓይነት ድርድሮች ሲካሄዱ የአንድን አገር ሉዓላዊነት እስከማስደፈር የሚደርሱ መሆን የለባቸውም።

በተጨማሪም ዕርዳታ ሰጪ አካላት የሚያስቀምጧቸው ቅድመ ሁኔታዎች በትክክል መጤንና መመርመር ይኖርባቸዋል። ዕርዳታዎች ስለመጡ ብቻ መቀበል ሳይሆን ትርፋማ መሆን ስለመቻሉ ትንታኔ መሠራት ይኖርበታል ሲሉ ገልፀዋል።

ባለፈው ሳምንት ዓለም ባንክ ለኢትዮጵያ በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት 5 ነጥብ 7 ቢሊዮን ዶላር ለመስጠት ቃል የገባ ሲሆን ፊላንድን ጨምሮ የተለያዩ ሀገራት በጦርነት ለተጎዱ አካባቢዎች ድጋፍ እያደረጉ ነው።

«ሕዝባችንን ከችግር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ማለት ማንዛቤን ማሳደግና የእይታ ከፍታን ማምጣት፤ በችግር ወቅት ከዳር ሁኖ ተመልካች መሆን ሳይሆን መሆን የሌለበት ጉዳይ ሲከሰት አይሆንም ማለት መቻል መሆኑን አብራርተዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቷ ገለጻ፤ ሕብረተሰቡ የተሟላ ሆስፒታል፣ ትምህርት ቤት፣ ውሃ፣ እና ሌሎች መሰረተ ልማት ስለሚያስፈልጉት መረባረብ ያስፈልጋል። ተመራቂ ተማሪዎች በትምህርት ያገኙትን እውቀትና ክህሎት ተጠቅመው ኢትዮጵያ ካለችበት ችግር እንድትወጣ የሚያስችሉ የመፍትሔ ሃሳቦችን ማፍለቅ ይጠበቅባቸዋል።

ኢትዮጵያ በበርካታ ችግሮች ውስጥ እያለፈች በመሆኑ በእውቀትና በክሕሎት የዳበረ ወጣት ትፈልጋለች ያሉት ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ፤ በተለይ ባለፉት ሁለት ዓመታት የታየው ደግሞ ፈጽሞ መፈጸም የለሌበት ድርጊት ነው። ደሃ ሕዝባችንን ካለበት ሁኔታ ለማውጣትና አገር ለማሳደግ መረባበርብ ሲገባን የበርካታ ዜጎቻችን ደም እንዲፈስ ተደርጓል። በርካታ አገሮች ከአገራቸው ወጥተው ዓለም አቀፍ አስተሳሰብ ላይ ባተኮሩበት ወቅት እኛ በቋንቋ፣ ብሔር ማንነት፣ በሃይማኖትና በሌሎች ተከፋፍለን ዜጎች በአሰቃቂ ሁኔታ እየተገደሉ መሆናቸው የሚያሳዝን መሆኑን ተናግረዋል።

መማር ማለት እያየን እንዳላየን መሆን አይደለም፤ ማሳለፍ የሌለብንን ዝም ብለን ማሳለፍ አይደለም ያሉት ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ፤ ተመራቂዎች ባሉበት ቦታ ሁነው ለአገር አንድነት፣ እድገትና ለውጥ እንዲሰሩ ጥሪ አስተላልፈዋል። መንግሥት ለተመራቂ ተማሪዎች የስራ እድል ለመፍጠር ጠንክሮ እንደሚሰራም ገልጸዋል።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ጣሰው ወልደሃና በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ ከውስጥና ከውጭ ጠላት በበዛባት ወቅት የተመረቃች በመሆኑ በዘርና በጎሳ ከመከፋፈል ወጥታችሁ ሀገራችሁን በጥናትና ምርምር መርዳት አለባችሁ ብለዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ፤ ዩኒቨርሲቲው ለ73ኛ ጊዜ በተለያዩ የትምህርት መስኮች ያስተማራቸውን 5 ሺህ 58 ተማሪዎች አስመርቋል። ከተመራቂዎቹ መካከል 2 ሺህ 420 በመጀመሪያ ዲግሪ እንዲሁም 2 ሺህ 438 ያህሉ ደግሞ በድህረ ምረቃ መርሐ ግብር ትምህርታቸውን የተከታተሉ ናቸው። ከድህረ ምረቃ ተመራቂዎች መካከል 131 ያህሉ በሦስተኛ ዲግሪ እንዲሁም 239 ያህሉ ደግሞ በስፔሻሊቲ መሆኑን ታውቋል።

«ኢትዮጵያ፣ ኤርትራና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የኢትዮጵያ፣ ኤርትራና ሶማሊያ ትብብር መጠናከር እንኳን ለራሳቸው አፍሪካ ውስጥ ለሚፈጠር ችግርም መፍቻ ይሆናል የሚሉት የፖለቲካ ተንታኙ ሀገራቱ በወቅታዊና ውስጣዊ ችግሮች ሳይዘናጉ ግንኙነታቸውን ማሳደግ ይኖርባቸዋል ብለዋል።

ምዕራባዊያን በቀይባህር እና በሕንድ ውቅያኖስ ያላቸውን ፍላጎት ለማስጠበቅ የቀንዱ ሀገራት ሰላም እንዲያጡ እንደሚያደርጉም ጠቅሰዋል።

ኢትዮጵያ፣ ኤርትራና ሶማሊያ የአፍሪካ ቀንድ የሚባለውን ቦታ ከየትኛውም ሀገር ይበልጥ በከፍተኛ ደረጃ የሚቆጣጠሩ ሀገሮች ከመሆናቸውም በተጨማሪ ኢትዮጵያ በሕዝብ ብዛት እና በቆዳ ስፋት ትልቋ መሆኗ ኤርትራና ሶማሊያ በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጣቸው ቀይባሕርና ሕንድ ውቅያኖስ አካባቢ ያለውን ትልቁን የባህር መስመር እስከ 5 ሺህ ኪሎ ሜትር ድረስ የሚሆን የባሕር መስመር ሁለቱ ሀገራት መቆጣጠራቸው የምዕራባዊያን ዓይን ከዚህ ቀጠና እንዳይነቀል ማድረጉንም ያነሳሉ።

ምዕራባዊያን ይህን ፍላጎታቸውን በቀጠናው ውስጥ በሚፈጠሩ ችግሮች ሰበብ አድርገው ለማስታረቅ በመግባት እንደሚጠቀሙበት የገለጹት ተንታኙ፤ የነዚህ ሀገራት ግንኙነት ችግሮቻቸውን በራሳቸው እንዲፈቱ ስለሚያስችላቸው ምዕራባዊያኑ ለማደናቀፍ እንደማይቦዝኑ ጠቁመዋል።

አቶ ኤፍሬም ለአብነት አንስተው እንዳብራሩት፤ ባለፉት ዓመታት ምዕራባዊያን በኢትዮጵያ ላይ ጫናቸውን ያበረቱት ከሕወሓት ጦርነት ጋር በተያያዘ ምክንያት ብቻ ሳይሆን የቀንዱ ሀገራት ትብብርም እየጨመረ መምጣቱ ስላሳሰባቸው ጭምር ነው። ሦስቱ የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት የሚያደርጉት የኢኮኖሚ፣ የቴክኖሎጂና ወታደራዊ ትብብር እነዚህን ሀገራት ራሳቸውን ወደ መቻል የሚያቀናቸውና ሌሎችንም ሀገራት በሂደት የሚጠቀልል ነው። የወታደራዊ ግንኙነት መኖሩ የቀጠናውን ሰላም በራሳቸው አቅም ያስከብራሉ፤ ይህ ደግሞ ለውትድርናው ዘርፍ፣ ለሰላም፣ ለንግድ እና ጠቅለል ብሎ ሲታይም አንድ ላይ ለማደግ ለሚደረገው ጥረት የነዚህ ሦስት ሀገራት ጥምረት ይጠቅማል።

ይህም ምዕራባዊያን በአፍሪካ ቀንድ ያላቸውን ጥቅምና ጣልቃ የመግባት ፍላጎት ስለሚያሳጣ የተለያዩ ጫናዎችን ሲያደርጉ ቆይተዋል፤ እያደረጉም ይገኛሉ ብለዋል።

ሆኖም የነዚህ ሦስት አገሮች ሕብረት ፈጥሮ በሰላምና በትብብር መኖር ተጠቃሚ የሚያደርገው ሁሉንም ሀገራት ነው። ሌላው ቀርቶ ሦስቱ ሀገራት ገበያ ሲጋሩ ራሳቸውን ወደ መቻል ይወስዳቸዋል። ቀጥሎም ወደ ምሥራቅና ወደ አጠቃላይ አፍሪካ ሊያድግ እንደሚችል አስረድተዋል።

ትብብራቸው የወታደራዊ ስምምነትንም የሚያካትት መሆኑ እና ኢትዮጵያና ኤርትራ ለረጅም ዘመናት አካባቢያቸውን አስከብረው የኖሩ የውጊያ ልምድም ያላቸው በመሆናቸው የምዕራባዊያን ሥጋት መጨመር ሌላው የሚጠቀስ ነጥብ ነው።

ይህንን ቀጣይ ለማድረግና ከግብ ለማድረስ ግን የአፍሪካ ትላልቅ ፖሊሲዎች የማይለዋወጡ መሆናቸውን በመጀመሪያ መረጋገጥ አለባቸው ይላሉ አቶ ኤፍሬም። አፍሪካውያን ትላልቅ የሚባሉ የአፍሪካ ፖሊሲዎች መሪዎች በተለዋወጡ ቁጥር እንደማይለዋወጡ ለምዕራባውያን ማሳወቅ እንዳለባቸውም ይገልጻሉ። ሶማሊያ በዚህ ግንኙነት ውስጥ የወሰደችው እርምጃ ትልልቅ የአፍሪካ ፖሊሲዎች መሪዎች በተለዋወጡ ቁጥር እንደማይለዋወጡ ያሳየ እንደሆነም ተናግረዋል።

ሕግን በማስከበርና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትሩ ዶክተር ለገሰ ቱሉ በኦሮሚያ ክልል ስራሮ ወረዳ ትናንት በተካሄደው የችግኝ ተከላ መርሃግብር ላይ እንደገለጹት፣ መንግሥት በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች ሕግና ሰላም ለማስከበርና ሁሉም ሕዝብ በልማት ስራዎች ላይ ትኩረት እንዲያደርግ ያላሰለሰ ጥረት እያደረገ ነው። በዚህም አመርቂ ውጤቶች እየተመዘገቡ ነው። በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች የአርሶ አደሩ መሬት፣ በቤተ እምነቶች ያሉና በየትምህርት ተቋማቱ ያሉ መሬቶች ጦም ሳያድሩ ምርት እንዲያመርቱ ከፍተኛ ርብርብ የተደረገ ነው። በየደረጃው ያሉ አመራሮችና የግብርና ባለሙያዎች ሕዝቡን እየደገፉ ነው።

በአንድ በኩል ሰላምና ሕግን እያስከበርን በሌላ በኩል ምርትና ምርታማነትን እያሳደግን ኢትዮጵያን የሚያበልጽግ ስራ እየሰራን ነው ያሉት ዶክተር ለገሰ፣ ከዚሁ ጎን ለጎን በአረንጓዴ አሻራ መርሃግብር አካባቢን የማልማት ስራ እየተሰራ መሆኑንም ገልጸዋል።

ችግኝ መትከል ብቻ ሳይሆን በመንከባከብ ለዘላቂ ልማትና ጥቅም እንዲውል ማድረግ እንደሚገባ አመልክተው፤ ሕዝቡ “በአንድ በኩል ሰላሙን እያስጠበቀ በሌላ በኩል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እየታተረ እና የጥገኝነትና የዘረኝነት አረም እየነቀለ ኢትዮጵያን በጋራ ለማልማት መትጋት እንደሚኖርበትም አሳስበዋል።

መንግሥት ሕግ የማስከበርና ምርትርና ምርታማነትን ለማሳደግ በትኩረት እየሰራ መሆኑን ጠቁመው፤ ለዚህ ደግሞ የሕዝቡ ተሳትፎ ከፍተኛ መሆን አለበት ብለዋል።

ሕዝቡ ጥገኝነት አስተሳሰብንና የጸረ ሰላም ሃይሎችን ሴራ በመንቀል ኢትዮጵያ እንድትበለጽግ የአካባቢውን ሰላም ከመጠበቅ ጎን ለጎንም ምርትና ምርታማነቱን ለማሳደግ በትጋት መስራት እንደሚኖርበትም ዶክተር ለገሰ ገልጸዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፣ ችግኝ መትከል የአካባቢን ሥነምህዳር ከመጠበቅ ባሻገር የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያግዝ ስለሆነ ሕዝቡ የተከላቸውን ችግኞች ተንከባክቦ ማሳደግ ይኖርበታል።

የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር መኩሪያ ሃይሌ በበኩላቸው፣ ካለፉት ሶስት ዓመታት በፊት አመራሩ ስለችግኝ ጥቅም ሲናገር ነበር። ካለፉት ሶስት ዓመታት ወዲህ ግን አመራሩ በተግባር ችግኝ ተክሎ በመንከባከብ እያሳየ ነው ብለዋል።

የተቀናጀ ችግኝ ተከላና ተፋሰስ እንዲኖር ማድረግ ተፈጥሮና የሰው ልጅ እየተመጋገቡ እንዲኖር የማድረግ ባህል አካል ነው ያሉት ኮሚሽነሩ፤ አሁን ላይ የአመራሩ ሚና ሕዝብን ማስተማር ብቻ ሳይሆን በተግባር ሰርቶ በማሳየት በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የተጀመረውን የአረንጓዴ አሻራ መርሃግብር ማሳካት እንደሚገባ ገልጸዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ተጠሪ ተቋማት በትናንትናው እለት አንድ ሰው 35 ችግኝ በድምሩ ከአምስት ሺ በላይ ችግኞችን ሲተክሉ በስራሮና በሻላ ወረዳዎች ለሚገኙ አቅመ ደካማ የሕብረተሰብ ክፍሎች ተማሪዎች የመማሪያ ቁሳቁስ ድጋፍ አድርገዋል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

ነፃ ሃሳብ

በቀምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቀምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኃን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

እየሆንለት ያለው ሁሉ ይገባዋል

(ክፍል ፪)

ታላቁ የኢትዮጵያ የሕዳሴ ግድብ የነገሮቻችን ሁሉ ወሳኝ መታጠፊያ/critical juncture/፤ የአህጉራችንን የጂኦ -ፖለቲክስ ሚዛን ፍጹም የሚቀይር ፤ ኢኮኖሚውን ይዞ የመነሳት አቅም ያለው ፤ አገራዊ አንድነት ለመፍጠር የማይተካ ሚና የሚጫወት ስለሆነ በክፍል አንድ መጣጥፌ ለመግለጽ እንደሞከርሁት እየሆነበንም ሆነ እየሆንለት ያለው ነገር ሁሉ ይገባዋል ስል ዛሬም አጽንኦት መስጠት እፈልጋለሁ።

ከአሜሪካው የካምፕ ዴቪድ ስምምነት በኋላ የግብፅና የእስራኤል ግንኙነት በመሻሻሉ፤ የወቅቱ የግብፅ ፕሬዚዳንት አንዋር ሳዳት የፍልስጤምና የእየሩሳሌም ችግር የሚፈታ ከሆነ ከአባይ ወንዝ 365 ሚሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ በየአመቱ ለእስራኤል ለመስጠት ቃል ገብተው ነበር። ይህ የጂኦ-ፖለቲካ የአሰላለፍ ለውጥ በራስጌ የተፋሰስ አገራት ላይ ውስብስብ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ አልቀረም። ሌላዋ የግርጌ ተፋሰስና ጎረቤት አገር ሱዳን ግድቦችን ገንብታለች። እአአ በ1926 ሴናርን ለመስኖ ፣ በ1936 ጀበል አውሊያ ለኃይል ማመንጫና ለመስኖ ገንብታለች። በ1950 3ኛውንና 420 ሺህ ሄክታር መሬት መስኖ የማልማት አቅም ያለው የሮሴሪስ ግድብን እንዲሁም ከእዚህ በተጨማሪ ሌሎች ግድቦችን ገንብታለች። በዚህም በመስኖ መልማት ከሚችለው 2 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሄክታር መሬቷ ነጥብ 9 ሚሊዮን ሄክታሩን ማልማት ችላለች። በግብፅና በሱዳን በመስኖ እየለማ ያለ መሬት የአባይን 86 በመቶ ከምታበረክተው አገራችን ጋር ስናስተያየው እዚህ ግባ የሚባል አለመሆኑ ሊያስቆጨን ይገባል ።

እንግዲህ ከፍ ብሎ እንደተመለከትነው በአባይ የውሃ ሀብት ላይ በብቸኝነት እየተጠቀሙ ያሉት ሁለቱ የግርጌ ተፋሰስ አገራት በተለይ ግብፅ ናት። በሌላ በኩል የራስጌ ተፋሰስ አገራት ኢትዮጵያን ጨምሮ የከፋ ድህነት ላይ እንደሚገኙ የተባበሩት መንግስታት የምግብና የግብርና ድርጅት /ፋኦ/ ይፋ ያረገው መረጃ ያመለክታል። ጥቅል የአገር ውስጥ ምርታቸው እጅግ ዝቅተኛ ከመሆኑ ባሻገር የምግብ ዋስትናቸውን ማረጋገጥ እንዳልቻሉ የመንግስታቱ ድርጅት ፋኦ ያትታል። በተፋሰሱ አገራት የሚገኝ አብዛኛው ሕዝብ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ አይደለም ። አማካኝ የአገራቱ ኤሌክትሪክ የማዳረስ ፍጥነት ከ30 በመቶ የተሻገረ አይደለም ። ከዜጋዋ ከ65 በመቶ የሚልቀው ሕዝቧ ለልጆቹ ማጥኛ ፣ ለቤተሰቡ ምግብ ማብሰያና ለምሽቱ ብርሃን የሚያገኝበት የኤሌክትሪክ ኃይል የለውም። ጸሎቱ የማታ እራትና መብራት አታሳጣኝ ቢሆንም አልሰመረለትም።

የውኃ ኃይል ማመንጫ በተለይ በራስጌ የተፋሰስ አገራት ለምቶ ጥቅም ላይ ባለመዋሉ በእድገታቸውና በልማታቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል። ይህ የኃይል እጥረት ዜጎች ፊታቸውን ወደ ከሰልና የማገዶ እንጨት እንዲያዞሩ በማድረጉ ከፍተኛ የደን ጭፍጨፋን ከማስከተሉ ባሻገር የመሬት መራቆት ፣ የአየር መዛባትንና ብክለትን እያስፋፋ ይገኛል። ለዚህ ነው በተመጣጣኝ ዋጋ ኃይል ማቅረብ የግድ የሆነው። የራስጌ አገራት ግብርና በዋናነት የዝናብ ጥገኛ ቢሆንም በተለይ ከቅርብ አመታት ወዲህ በአየር ፀባይ ለውጥ የተነሳ በየአመቱ ሊባል በሚችል ሁኔታ ድርቅ ስለሚከሰት የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ፈተና ከሆነ ውሎ አድሯል። ስለዚህ እንደ መስኖ ያለ አማራጭ የውሃ ሀብቶችን በመጠቀም ምርታማነትን ማሳደግ የህልውና ጉዳይ ነው። የናይልን የውሃ ሀብት በፍትሐዊነትና በኃላፊነት የመጠቀም ጉዳይ ከአመት አመት እየገፋ ከመምጣቱ ባሻገር የተግባር እንቅስቃሴ ተጀምሯል።

ታንዛኒያ ከቪክቶሪያ ሀይቅ 170 ኪሎ ሜትር በተዘረጋ ቧንቧ ውሃ በመውሰድ በአገሪቱ በከፋ ድህነት የሚታወቀውን ካሃማ የተባለውን አካባቢ በመስኖ ለማልማት እየተንቀሳቀሰች ነው። ሌሎች የራስጌ ተፋሰስ አገራትም ከወንዙ ድርሻቸውን በመጠቀም የውሃ ኃይል ማመንጫና የመስኖ ግንባታዎችን በማካሄድ ርሀብንና ድህነትን ለመዋጋት ቆርጠው ተነስተዋል ። ለአባይ ወንዝ ውሃ 86 በመቶውን የምታበረክተው አገራችን ኢትዮጵያ ታላቁን የሕዳሴ ግድብ የምትገነባው ከከፋ ድህነት ለመውጣትና የተፈጥሮ ሀብቷን የመጠቀም ሉዓላዊ መብቷን ለማረጋገጥ ነው ። የተለያዩ የጥናትና የምርምር ወረቀቶች አገራችን ኢትዮጵያ በመስኖ መልማት የሚችል 3 ነጥብ 7 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ሲኖራት ከዚህ ውስጥ ግማሽ ያህሉ መሬት የሚገኘው በአባይ ተፋሰስ ነው። የሚያስቆጨው እስካሁን የለማው ከ6 በመቶ አለመብለጡ ነው።

ኢትዮጵያ እስካሁን ያለማችው ከ250ሺህ ሄክታር መሬት በላይ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የአባይ ተፋሰስ ድርሻ ከ20ሺህ ሄክታር አይበልጥም። የአገራችን ግብርና የዝናብ ጥገኛ ነው። ኢትዮጵያ የአፍሪካ የውሃ ማማ በመባል ብትታወቅም በየአመቱ ሊባል በሚችል ሁኔታ በድርቅ እየተጠቃች ነው። በየአስር አመቱ ይከሰት የነበረው ድርቅ በበልግና በመኸር በአመት ሁለት ጊዜ ሲጎበኘን እየተመለከትን ነው። ይህ ያልተስተካከለና የሚቆራረጥ ዝናብ የሚያስከትለው ድርቅ ሚሊዮኖች ለምግብ እጥረት እንዲዳረጉ ምክንያት እየሆነ ነው።

በውል እንደሚታወቀው አገራችን ከግብፅም ሆነ ከሱዳን ጋር የአባይን ወንዝ በጋራ መጠቀም የሚያስችል ስምምነት የለም። ሆኖም ለናይል ወንዝ 86 በመቶውን ውሃ የምታበረክተው ኢትዮጵያ በ1929ኙም ሆነ በ1959ኙ የቅኝ ገዢ ስምምነት እንደማትገዛ በየአጋጣሚው ከማሳወቅ ባሻገር እውን ሳይሆን ቢቀርም ከ1950ዎቹ ጀምሮ የኃይል ማመንጫና የመስኖ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ተደጋጋሚ ጥረት ስታደርግ ቆይታለች።

እ.ኤ.አ ከ1958 እስከ 1963 ድረስ አሜሪካ እንዲህ እንደ ዛሬው የግብፅ ጥቅም አስከባሪ ሳትሆን የአባይን ወንዝ ለማልማት በሚደረጉ ጥረቶች ግንባር ቀደም ተዋናይ ነበረች። ዘላቂ ጥቅም እንጂ ዘላቂ ወዳጅ የለም እንዲሉ። የዛሬውን ታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ጨምሮ 33 የመስኖና የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶችን አጥንታ እንዲለሙ ምክረ ሀሳብ አቅርባ ነበር። ከእነዚህ ጥናቶች ስራ ላይ የዋለው እ.ኤ.አ በ1972 ዓ.ም የተገነባውና 128 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያመነጨው የፊንጫ የውሃ ኃይል ቀዳሚ ነው ማለት ይቻላል።

ኢትዮጵያ በአንድ በኩል ድርቅ በሌላ በኩል ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት እንደ ውጋት ቀስፈው ይዘዋታል። ከዚህ ውጋት ተንፈስ ለማለት የውሃ ሀብቷን አልምታ መጠቀም አለባት። የመስኖ መሰረተ ልማትን በማስፋት እያደገ የመጣውን የምግብ ፍላጎቷን በማሟላት ሕዝቧን ከተመፅዋችነት ማላቀቅ ይጠበቅባታል። ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ለምታደርገው ሽግግር እና በኩራዝ ጭስ ለሚጨናበሰው 68 ሚሊዮን ሕዝቧ የኤሌክትሪክ ኃይልና መብራት ለማቅረብ እንደ አባይ ያሉ አመቱን ሙሉ የሚፈሱ ወንዞቿን ገድባ መጠቀም የሞት ሽረት ትንቅንቅ እየሆነ መጥቷል።

ከዚህ ከፍ ሲልም ኢትዮጵያ ለተፋሰሱ አገራት የኃይል አማራጭ የመሆን እምቅ የተፈጥሮ ፀጋ አላት። ይሁንና እስከ ቅርብ አመታት ድረስ በድህነቷ እንዲሁም ከአለማቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ብድርና ድጋፍ ለማግኘት የምታደርገው ጥረት በግብፅ የተቀናጀ ስውርና ይፋ ዲፕሎማሲያዊ ዘመቻ የተነሳ እቅዷ ሁሉ ይጨናገፍባት ስለነበር ግዙፍ የውኃ ኃይል ማመንጫዎችንና ታላላቅ የመስኖ መሰረተ ልማት ግንባታዎችን ማካሄድ ስላልቻለች በከፋ ድህነት በመማቀቅ ላይ ትገኛለች።

የሚያሳዝነው ለኢትዮጵያ ሲሆን የሚታጠፈው የአለማቀፍ የፋይናንስ ተቋማት እጅ ለግብፅ ሲሆን ግን ያለስስት ይዘረጋል። ለጋስ ይሆናል። ግብፅ ይህን በመጠቀም ኢኮኖሚዋን ማሳደግ ችላለች። የአገር ውስጥ ጥቅል ምርቷ 235 ቢሊዮን ዶላር ሲሆን፤ የዜጎቿ የነፍስ ወከፍ ገቢ 2ሺህ 440 ዶላር ደርሷል። የኢትዮጵያ ጥቅል የአገር ውስጥ ምርት 8ነ ቢሊዮን 76 ሚሊዮን ዶላር ሲሆን የነፍስ ወከፍ ገቢዋ ደግሞ ወደ 1000 ዶላር ይጠጋል።

ከዚህ የድህነት አረንቋ ወጥቶ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ለመሰለፍ የተፈጥሮ ሀብቷን በተለይ የውሃ ሀብቷን በአግባቡ ማልማት ይኖርባታል። ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ በ2025 ዓ.ም ከግብፅ በላይ የሕዝብ ብዛት ይኖራታል ተብሎ ተተንብዮል። በዘወርዋራ ምግብና የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያስፈልገው ሕዝብ ቁጥር አሁን ካለው ይጨምራል ማለት ነው። ከግብፅ በላይ የውሃ ሀብቷን ለመስኖና ለኃይል ማመንጫ መጠቀም ይኖርባታል ማለት ነው። በግዛቷ ስር ያለ የውሃ ሀብቷን መጠቀም ደግሞ ሉዓላዊ መብቷ ነው።

ሆኖም የፋይናንስ እጥረትና የቴክኖሎጂ ውስንነት ዘረፉን ለማልማት የተያዘውን እቅድ ፈታኝ ቢያደርገውም ተጨማሪ የውሃ ኃይል ማመንጫዎችንና የመስኖ አውታሮችን መገንባት ቅድሚያ የተሰጠው ተግባር ሆኖ ይቀጥላል። ቁልፉ የእድገትና የልማት ግብ በአጭር ጊዜ ውስጥ በሁለንተናዊ መልኩ ድህነትን መቅረፍ ነውና። በ2003 ዓ.ም ከሱዳን ድንበር 40 ኪሎ ሜትር ርቀት ጉባ ላይ ግንባታው የተጀመረውና ለኃይል ማመንጫነት የሚውለውና 74 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ የሚይዘው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ እድገትንና ልማትን በማፋጠን ዜጎችን ከድህነት የማላቀቅ ራእይ ሰንቋል። ግድቡ በቀን 6ሺህ ሜጋ ዋት ፣ በአመት 15ሺህ 130 ጊጋ ዋት ኃይል የማመንጨት አቅም አለው። በዚህም የአገር ውስጥ የኤሌክትሪክ ኃይል ፍላጎትን በማርካት ለምስራቅ አፍሪካ በተለይ ለራስጌ ተፋሰስ አገራትም የማቅረብ እቅድ አለው።

ግድቡ በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኘውን የንጹህ ኃይል ተደራሽነት ያሳድጋል። የዓለም ባንክ ጥናት እንደሚያመለክተው ከሰሀራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገራት ከሰሀራ በታች ያሉ አገራት የኤሌክትሪክ ሽፋን 24 በመቶ ፤ የኢትዮጵያ ከ45 በመቶ ያልበለጠ ፣ የሱዳን ከ57 በመቶ ያልበለጠ ሲሆን የግብፅ ሽፋን ግን 100 በመቶ ደርሷል። በናይል ውሃ አጠቃቀም ላይ ግብፅ የቅኝ ግዛት ዘመን ስምምነቶችን በመጥቀስ ብቸኛ ባለመብትና ተጠቃሚ እኔ ነኝ በማለት የያዘችው ግትር አቋም ፤ የራስጌ አገራት በአለማቀፍ ሕግ የተረጋገጠላቸውን ውሃውን በፍትሐዊነት የመጠቀም ተፈጥሯዊ መብት የሚጥስ ስለሆነ በንግግርና በውይይት ካልተፈታ ለግጭት ሊዳርግ ይችላል ተብሎ እየተሰጋ ይገኛል ።

ይሁንና ግጭትንና አለመግባባትን ለመፍታት ሰባቱ የራስጌ የተፋሰስ አገራት የቅኝ ግዛት ዘመን ስምምነቶች ፍትሐዊ ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ አዳዲስ ውሎች ሊተኩ እንደሚገባ የሚጠይቀውና በ2002 ዓ.ም የተፈረመውን የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት Cooperation Frame Work Agreement (CFA) ስራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል። ስምምነቱን የተፈራረሙ አገራት ብሩንዲ፣ ኬንያ፣ ኡጋንዳ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ታንዛኒያና ሩዋንዳ ሲሆኑ የትብብር ማዕቀፉ የናይልን ወንዝ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ መጠቀምን የሚያረጋግጥና ዋስትና የሚሰጥ ቋሚ ኮሚሽን እንዲቋቋም የሚጠይቅም ነው። ዳሩ ግን ሱዳንና ግብፅ ይህን የትብብር ማዕቀፍ ለመፈረም ፈቃደኛ ባይሆኑም በ2007 ዓ.ም በግብፅ ፣ በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል የተፈረመውን የመርሆዎች መግለጫ (Declaration of Principles) ፈርመዋል።

በዚህ ስምምነት ሱዳንና ግብፅ የህዳሴ ግድብ ፕሮጀክትን የተቀበሉ ሲሆን ኢትዮጵያም ግድቡ በግርጌ ተፋሰስ አገራት ማለትም በግብፅና በሱዳን ሊያሳድረው የሚችል ተፅዕኖ ወይም ጉዳት ካለ ጥናት እንዲደረግ ተስማምታለች። በዚህ ስምምነት ላይ ተከታታይ ውይይቶች የተካሄዱ ሲሆን ተስፋም ተጥሎባቸው ነበር። የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ለቀጠናዊ ትብብር አብነት የሚሆንና የራስጌ አገራትን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፕሮጀክት ስለሆነ ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ድጋፍ ሊደረግለት ይገባል። ግብፅም በግድቡ ውሃ አሞላል ላይ ከኢትዮጵያ ጋር ጀምራ ወደነበረው ድርድር ብትመለስ አገራቱን ተጠቃሚ ማድረግ የሚችል መግባባት ላይ መድረስ ይችላል።

እንደጀመርን እንጨርሰዋለን !
አሜን ።

ማህበራዊ

የሕይወት ገጽታ

"የህክምና ሙያ ፍቅር የሚጠይቅ በመሆኑ በገንዘብ መተመኑ ከባድ ነው"

ፕሮፌሰር ይልቃል አዳሙ
የዓይን ህክምና ስፔሻሊስትና መምህር

እፀገነት ሸክሲቡ

የትኛውም ልጅ በልጅነቱ ስታድግ ምን መሆን ትፈልጋለህ? ተብሎ ሲጠየቅ ዶክተር፣ ፓይለት፣ አስተማሪና ሌሎችንም ይላል። የሕይወት መንገድ የቀናቸው የተመኙትን ሊሆኑ ይችላሉ። አብዛኞቹ ግን ህልምና ኑሮ ላይገናኝላቸው ይችላል። ያም ሆኖ ግን በልጅነት ህልምን ማስቀመጥ ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም። የዛሬ የሕይወት ገጽታ አምድ እንግዳችን በልጅነት ዘመናቸው ይህንን እሆናለሁ ብለው ባያስቡም የሕይወት አጋጣሚ የኑሮ መንገድ መራቸውና ዛሬ ላይ አንቱ ያስባላቸውን ብሎም ለብዙዎች ብርሃን እንዲሆኑ ያስቻላቸውን የህክምና ሙያ ውስጥ ገቡ። የሰዎችን ሁለንተናዊ ኑሮ የሚያዘውን የዓይን ሕክምና ባለሙያ የሆኑት ፕሮፌሰር ይልቃል አዳሙ ይባላሉ።

ፕሮፌሰር ይልቃል አዳሙ ተወልደው ያደጉት በድሮ ጎጃም ክፍለ ሀገር ቆላ ዳሞት አውራጃ ቋሪት ወረዳ ዘጌ ፅዮን ቀበሌ ነው። ለቤተሰባቸው ያሉትንም የሞቱትንም ቆጥረው ስድስተኛ ልጅ መሆናቸውን ይናገራሉ።

የአርሶ አደር ልጅ የሆኑት ፕሮፌሰር ይልቃል ትምህርት ለመጀመር ከቀያቸው ርቀው መሄድ ነበረባቸው ነገር ግን ቤተሰቦቻቸውም ለትምህርት ዋጋ በመስጠት ርቀው ሄደው እንዲማሩ እድል አመቻቹላቸው እሳቸውም በወረዳው ብቸኛ በነበረው ቋሪት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ገብተው የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ሆነ።

" .....እኔ እድሜዬ ለትምህርት ሲደርስ በምኖርበት ወረዳ ላይ በተለይም ለቤተሰቦቼ ቅርብ በሆነ አካባቢ ላይ ትምህርት ቤት አልነበረም፤ ይህ ደግሞ ከቤተሰቤ ርቄ ሄጄ ትምህርቴን እንድከታተል አስገደደኝ። በመሆኑም ገና 10 ዓመት እንኳን ሳይሞላኝ ዘመድ ቤት ሆኜ ትምህርቴን መከታተል ተገደድኩ" ይላሉ።

በዚህ ሁኔታም ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ያለውን ትምህርታቸውን በሦስት ዓመት አጠናቀው እንደ አጋጣሚ ሆኖ እሳቸውና ጓደኞቻቸው ወደ ሰባተኛ ክፍል በሚያልፉበት ጊዜ ትምህርት ቤቱ ክፍሎች ጨምሮ ሰባተኛና ስምንተኛ ክፍልን እንዲያስተምር ተወሰነለት፤ ፕሮፌሰርና ጓደኞቻቸውን ሰባተኛና ስምንተኛ ክፍልን ለመማር ሩቅ ከመሄድ ተገላገሉ።

".....በወቅቱ ትምህርት ቤቱ እስከ ስድስተኛ ክፍል ብቻ ነበር የሚያስተምረው ነገር ግን የእድል ነገር ሆኖ እኛ ወደ ሰባተኛ ክፍል ስናልፍ ትምህርት ቤቱም ሰባተኛን እንዲያስተምር ሆነ። በዚህ ጊዜም እኛ ተማሪዎቹ ገንዘብ በማዋጣት ተጨማሪ ሁለት ክፍሎች እንዲሰሩ ተደረገ። በዚህም አንዱን ክፍል ሰባተኛን ከተማርንበት በኋላ በቀጣዩ ዓመት ደግሞ አንዱን ክፍል ስምንተኛ ክፍልን ተማርንበት" ይላሉ ሁኔታውን በማስታወስ።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውንም ለመቀጠል ወደ አውራጃው ትምህርት ቤት መሄድ ነበረባቸውና ወደዛ ሄዱ። ነገር ግን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በወጉ እንዳይማሩ ያደረጋቸው ሁኔታ ተፈጠረ ይኸውም የአባታቸው ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ነበር። ስለዚህም የዘጠነኛ ክፍል ትምህርታቸውን ለአንድ አመት አቋረጡ፤ በኋላም እንደገና የዘጠነኛ ክፍል ትምህርታቸውን ለመከታተል ወደ ትምህርት ቤት ተመለሱ።

"....የአባቴ መሞት የዘጠነኛ ክፍል ትምህርቴን ለአንድ ዓመት እንዳቋርጥ አስገደደኝ ። እናቴ ያለአባት ብዙ ልጆችን ማሳደግ ስለነበረባት እኔም ከትውልድ አካባቢዬ ርቄ ስለሄድኩ ትምህርቴን በአግባቡ ለመከታተል ከፍ ያለ ችግር ውስጥ ነበርኩ " ይላሉ ።

ሳይደግስ አይጣላም ነውና ብሂሉ ፕሮፌሰር ይልቃል የዘጠነኛ ክፍል ትምህርታቸውን የመጀመሪያ መንፈቅ ዓመት እንዳጠናቀቁ የስራ ማስታወቂያ አዩ እድሜያቸው ለስራ ያልደረሰም ቢሆን ስምንተኛ ክፍልን ያጠናቀቀ ይል ስለነበር እድሜያቸውን ከፍ አድርገው ለውድድር ተመዘገቡ።

".....የተመዘገብነው ስራ የጤና ረዳት የሚል ነበር። በወቅቱ ፈንጣጣ ከአገራችን የጠፋበት ጊዜ ስለነበር እና፤ የዓለም ጤና ድርጅት ለጤና ጥበቃ እርዳታ በመስጠት በዚህ ዘመቻ የተሳተፉትን ወጣቶች በብዛት በጤና ረዳትነት እንዲሰለጥኑ ሲደረግ ፤ ጤና ጥበቃ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ከየትምህርት ቤቱ ፤ ከጦር ሰራዊት፤ ከፖሊስ፤ ከመንግስት እርሻዎችና ከተለያዩ ቦታዎች ወጣቶችን መልምሎ በጤና ረዳትነት ለማሰልጠን የወጣ ማስታወቂያ ነበር። በወቅቱም ውድድሩን በማለፌ ለስልጠና ታጠቅ ጦር ሰፈር ገባሁ" ይላሉ።

ስልጠናውን ለአንድ ዓመት ያህል ከወሰዱ በኋላ በቀጥታ የተመደቡት 155 ብር ደመወዝ ጎንደር ክፍለ ሀገር ሁመራ ሆስፒታል ነበር። ቀስ ብሎም ደመወዛቸው ወደ 182 ብር ከፍ አለላቸው። በዚህ ሆስፒታል ላይ ለሶስት ዓመት ያህል ሰሩ። እንዳሰቡትም እናታቸውን ለመደገፍ እድሉን አገኙ።

" ....የጤና ባለሙያ እሆናለሁ ብዬ በልጅነቴም አልተመኘሁም እንደውም እኔ አስብ የነበረው የሒሳብ ትምህርት እወድ ስለነበር የኢንጂነሪንግ ተማሪ እሆናለሁ ብዬ ነበር። ነገር ግን ጤና ረዳትነትን ስማር በተለይም ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ልምምድ ሳደርግ የህክምና ተማሪዎችንና መምህራኖቻቸውን በቅርብ የማየት እድል ሳገኝ ለሙያው ፍቅርና ቅናት አደረብኝ። በትምህርቴም ጥሩ ስለነበርኩ መምህራኖቼም በዚሁ መቅረት እንደሌለብኝ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ሊያዩን እንደሚፈልጉ ደጋግመው ይነግሩኝ ስለነበር ሐኪም መሆን እንዳለብኝ ያን ጊዜ ነው የወሰንኩት" ይላሉ።

ፕሮፌሰር የህክምናን ሙያ ካዩት በኋላ ራሳቸውን አሻሽለው ትልቅ ደረጃ መድረስ እንዳለባቸው ወሰኑ። ይህንንም ለማሳካት ቤተሰባቸውን እየረዱ ራሳቸውን እያሻነፉ ብዙ ትግል አደረጉ። ፕሮፌሰር መሻሻልን ስንቅ ስላደረጉ በስራ ቦታቸው ተመድበው እየሰሩ በተልዕኮ ትምህርት ከዘጠነኛ እስከ 11 ክፍል ያለውን ትምህርታቸውን ቀጠሉ።

የሁመራ ቆይታቸውንም አጠናቀው በጭልጋ አውራጃ አይከል ጤና ጣቢያ ተቀየሩ። ይህ ሁኔታ ግን ፕሮፌሰር ላይ ቅሬታን ፈጠረ ፤ ምክንያቱም ሁመራ ላይ ሶስት ዓመት ስለሰሩ ይጠብቁ የነበረው ዝውውር ጎንደር ወይም ደብርታቦር ከተሞች ላይ ነበርና ቅር አላቸው። ያም ቢሆን ግን ወደተመደቡበት አካባቢ ሄደው ለስድስት ወራት ስራቸውን ሰሩ። ከዛ ግን ስራቸውን ትተው ወደ ባህርዳር በመሄድ ጣና ሐይቅ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመግባት የ12ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በመደበኛው መርሀ ግብር አጠናቀቁ።

".....ትምህርቴን ከዘጠነኛ ክፍል አቋርጬ ወደስራ ከገባሁ ጀምሮ ቢያንስ እናቴን ምንም ነገር አላስቸገርኩም ፤ ራሴን ችያለሁ፤ ሁለተኛ ደግሞ ሁመራ ላይ የበረሃ አበልም ስለነበረው ፤ በባህርዬም ቁጥብ ስለሆንኩ ገንዘቡን በአግባቡ አጠራቅሜ ከሁለት ዓመት በኋላ ቤተሰቤን ለመጠየቅ ስመለስ ልብስ ገዝቼ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ አድርጌ በጣም ተደስተው ነበር። እንደውም የአካባቢያችን ሰዎች ይልቃል "አካባቢውን የሃብታም ፍየል አስመሰለው" እስኪባል ድረስ አዘንጫቸው ነበር፤ በመሆኑም ጤና ረዳት መሆኔ በጣም ጠቅሞኛል" ይላሉ።

ፕሮፌሰር ይልቃል በዛ በለጋ እድሜያቸው የሰሩትን የጤና ረዳትነት ስራ እስከ አሁን ላለው ሕይወታቸው እጅግ እንደጠቀማቸው ነው የሚናገሩት። ምክንያቱም ገና በልጅነታቸው ብዙ ጠንካራ ውሳኔዎችን እንዲወስኑም ስለማስቻሉ ነው የሚናገሩት።

"..... የጤና ረዳት ሆኜ ስራ የጀመርኩት ከ18 ዓመት በታች በነበረ እድሜዬ ነው። በዛን ወቅት ደግሞ ራሴን ችዬ በርካታ ጠንካራ ውሳኔዎችን ወስኛለሁ። ምናልባት አሁን ቢሆን የማልደፍራቸውን ውሳኔዎች ወስኛለሁ። ለምሳሌ ትምህርቴን አቋርጬ ወደስራ የገባሁት ማንንም ሳላማክር በራሴ ውሳኔ ነው። ስራዬን ትቼ ባህርዳር የ12ኛ ክፍል ትምህርቴን የተከታተልኩት ለማንም ሳልናገር ነው። እነዚህ ሁሉ ለእኔ በእድሜዬ ትልልቅ ውሳኔዎች ናቸው"።



ፎቶ : በፀሐይ ንጉሴ

የህክምና ስራ ማስት እንደማንኛውም የቢሮ ስራ ተጥሎ የሚወጣ ነገ እጨርሰዋለሁ የሚባል አይደለም፤ አብሮ ቤት ድረስ የሚሄድ፤ ዛሬ እረፍት ሳይ ነኝ አልሰራም፤ ተኝቻለሁ አልቀሰቀስም፤ ማለት የማያስችል ነው:: በመሆኑም ሐኪም የራሱን ምቾት እያሰበ ህክምና እሰራለሁ ካለ አይሆንም፤ በመሆኑም ስስራው እራስን ያለምንም ስሴት መስጠት ይጠይቃል

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውንም በጥሩ ውጤት በማጠናቀቅ ጎንደር የህክምና ሳይንስ ኮሌጅ ተመደቡ። ብልሁ ይልቃልም በስራ ላይ እያሉ ያፈሩትን ንብረት በመሸጥና ገንዘቡን ባንክ በማስገባት እየቆጠቡ ራሳቸውን እየረዱ የሕክምና ትምህርታቸውን መማራቸውን ይናገራሉ። በዚህች ባስቀመጧት ገንዘብም በሳቸው ደረጃ እንደልብ በሚባል መልኩ ለእስክርቢቶ ፤ ለወረቀት፤ ለልብስና ለጫማ መግዣ ሳይቸገሩ መማራቸውን ይናገራሉ።

ሕይወቴን የመራሁት በጣም በዕቅድና በፕሮግራም ነው የሚሉት ፕሮፌሰር ይልቃል ይህንን ዓይነት ሰው እንድሆን እድሉን የከፈተልኝ ደግሞ ጤና ረዳትነት ስልጠና መሄዴ ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ ብዙ እቸገር ነበር በማለት ይናገራሉ።

በጎንደር ሕክምና ሣይንስ ኮሌጅ (ያኔ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስር እንደነበረ ልብ ይሏል) ሕክምናን የተማሩት ፕሮፌሰር ይልቃል የትምህርት ቆይታቸውም ጥሩ እንደነበር ይናገራሉ። እንደውም መጀመሪያ የጤና ረዳትነት ስልጠናን መውሰድዎ ምን ያህል አገዘዎት ጎበዝ ተማሪ አደረገዎት? ብዬ ላነሳሁላቸው ጥያቄ ሲመልሱም "...ስልጠናው አግዞኛል ለማለት አያስደፍርም፤ ግን ደግሞ ለትምህርቱ እንግዳ እንዳልሆን አድርጎኛል ፤ እኛ በጤና ረዳትነት 1 ዓመት የሰለጠነውን ዩኒቨርሲቲው ላይ በአንድ ቀን ልንማረው እንችላለን። ነገር ግን 12ኛ ክፍልን ተፈትነው በቀጥታ ዩኒቨርሲቲውን ከተቀላቀሉት ተማሪዎች እንሻል ነበር፤ ውጤት እስከመቀየር ድረስ የሚያደርስ ግን አልነበረም" ይላሉ።

በህክምና ትምህርት ቤት ውስጥ የነበራቸው ውጤት

ማህበራዊ

የሕይወት ገጽታ

መካከለኛ ነበር። ስራ ላይ የነበሩ መሆናቸው ደግሞ ብዙ እንዳይጨነቁ እባረራለሁ ብለው ሰግተው ሌት ተቀን እንቅልፋቸውን እንዳያጡ አድርጓቸዋል፤ ይህም ቢሆን ግን ዝቅ ያለ ውጤትም ላለማምጣት የቻሉትን ያህል ያጠኑም ነበር።

የጎንደር ሕክምና ሣይንስ ኮሌጅ የህክምና ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ የተመደቡት ከንባታና ሃድያ አውራጃ ውስጥ ሸንሸቾ ጤና ጣቢያ ነው። ባለ ብዙ እቅዱ ፕሮፌሰር ይልቃል እዚህ ቦታ ላይ ከ26 ቀን በላይ መስራት አልቻሉም። ምክንያቱ ደግሞ ወደ ኤርትራ ዝመት መባላቸው ነበር። ነገር ግን በተፈለጉበት ሰዓት መድረስ ባለመቻላቸው ሌላ ሰው ተላከ። ይህ ዘመቻ ቢያልፋቸውም ለሌላ ዘመቻ ታጠቅ ማገገሚያ ማዕከል እንዲዘምቱ ሆነ። በዚህ ቦታ ላይ ሶስት ያህል ወራቶችን እንደሰሩ ኢህአዴግ አገሪቱን በመቆጣጠሩ ታጠቅን ለቀው አዲስ አበባ ገቡ።

በወቅቱ ስድስት ኪሎ ፖለቲካ ትምህርት ቤት (አሁን የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋኩሊቲ) ተብሎ በሚታወቀው ግቢ ውስጥ የደርግ ባለስልጣናት በእስር እንዲቆዩ ተደረገ፤ በግቢው ውስጥ የነበሩት የጦር ምርኮኞች ወደሌላ ማገገሚያ እንዲሄዱና እሳቸው ደግሞ እዛው ጤና ጣቢያ በማቋቋም የደርግ ባለስልጣናትን እንዲያክሙ ሆነ።

"..... አዎ በወቅቱ በስድስት ኪሎ ፖለቲካ ትምህርት ቤት ቁስለኞችን አክም ነበር፤ ነገር ግን የመንግስት ለውጥ በመደረጉ ቦታው ላይ የደርግ ባለስልጣናት እንዲገቡና ቁስለኞቹ ወደሌላ ማገገሚያ ማዕከል እንዲዞሩ ሆነ። እኔም እዛው ጤና ጣቢያ አቋቁሜ ባለስልጣናቱን ለስድስት ወራት ያህል እያከምኩ ከቆየሁ በኋላ ሰንዳፋ ወደሚገኘው የኢትዮጵያ ፖሊስ ኮሌጅ እንድንዞር ተደረገ" ይላሉ።

ከእነዚህ አገርን ሲመሩ ከነበሩ እሳቸውም ሆነ አብዛኛው ህዝብ በሩቅ እንጂ በቅርብ አይቷቸው አግኝቷቸው ከማያውቅ የደርግ ባለስልጣናት ጋር ሦስት አመታት በህክምና ሙያቸው የማገልገል እድልንም አግኝተዋል።

"...በወቅቱ ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም እና ጣሊያን ኤምባሲ ከተጠለሉት በቀር ሁሉም የእኔው ታካሚ ነበሩ። እነ ሻምበል ፍቅረ ስላሴ ወግደረስ፣ ሌተናል ኮሎኔል ፍሰሃ ደስታን ጨምሮ ብዙዎቹ በስም የምናውቃቸው ሁሉ ነበሩ። ከመቶ በላይ ጀነራሎችና ሚኒስትሮችም እንደዛው። በእድሜ ልጅ(ወጣት) ስለነበርሁ ብዙዎቹ በስራዬ ላይ ሲያዩኝ ታግዬ ከኢህአዴግ ጋር የመጣሁ ስለምመስላቸው በጣም ይጠነቀቁ እንደነበር በኋላ አጫውተውኛል"።

አገሪቱን በከፍተኛ የስልጣን እርከን ላይ ሆነው ሲመሩ የነበሩ ሰዎች ከፍተኛ የጦር ጀነራሎችና ሌሎችንም ማከም ለእርስዎስ ምን ስሜትን ፈጠረብዎት? ስላቸው "..... እነሱ ትልቅ መሆናቸው የሚፈጥረው ስሜት እንዳለ ሆኖ እኔ ልጅ ሆኜ የተወለድኩበት ወረዳ ሲያምጽ ከመንግስት ጋር ተዋግቷል፤ አባቴ የሞተው በዚሁ ምክንያት ነው፤ ስለዚህ የደርግ ስርዓት አባቴን ገሎብኛል ማለት ነው ፤ እነዚህ ሰዎች ደግሞ በቀጥታ አባቴን ባይገሉትም በስርዓቱ ውስጥ የነበሩ ናቸው የአባቴ ገዳዮች ነበሩ፤ ይህም ቢሆን ግን ለራሴ ደጋግሜ እነግረው የነበረው በእኔና በቤተሰቤ ላይ የደረሰውን ነገር ሁሉ ረስቼ በሙያዬ የሚፈልጉትን አገልግሎት መስጠት እንዳለብኝ ነበር፤ በመሆኑም የልቤ ሀዘን ተጽዕኖ አድርጎብኝ የገባሁትን ቃል ኪዳን እንዳላፈርስ ጥንቃቄ አደርግ ነበር" ይላሉ ሁኔታውን ሲያስታውሱ።

ይህ የልባቸው መሻት ተሳክቶላቸውም ባለስልጣናቱን ለሶስት አመታት ያለምንም ችግር የጤና ሁኔታቸውን ሲከታተሉ የባሰ ነገርም ሲያዩ ተጨማሪ ህክምናን እንዲያገኙ ወደ ሆስፒታሎች ሲልኩ በባለስልጣናቱም አብዝቶ ሲወደዱና ሲመሰገኑ ቆዩ። በዚህ ሙያዊ ስነ ምግባራቸው ደግሞ እስከ አሁንም ድረስ ሲያገኟቸው በፍቅር የሚያዩቸው ተደዋውለው የሚጠያየቁ ቤተሰቦችን ለመፍራት ችለዋል።

ፕሮፌሰር ባለስልጣናቱን እያገለገሉ ባሉበት ወቅት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ጳውሎስ እስረኞቹን ለመጎብኘት ወደ ስፍራው ይሄዳሉ ፤ በወቅቱ ያሏቸውን ነገር እስከ አሁን ድረስ ያስታውሳሉ፤" .....አቡነ ጳውሎስ አስረኞቹን ለመጎብኘት ወደ ስፍራው መጡ እነሱን ጎብኝተው ከጨረሱ በኋላ እኔን ጠርተው አንተ እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች እንድትንከባከብ እንድታገለግል መርጦሃል ፤ እነዚህ ሰዎች እራሳቸውን መከላከል የማይችሉ በሰው ቁጥጥር ስር ያሉ ስለሆኑ ከፍተኛ እንክብካቤ ይፈልጋሉ አንተም ይህንን እንድታደርግ " ብለውኝ ሲሄዱ በእውነት ትልቅ ሃላፊነት ነበር የተሰማኝ ያንንም ለመወጣት የምችለውን ሁሉ አድርጌያለሁ" ይላሉ።

".....እነሱን ማየት ማናገር እንደሚፈልግ እንደማንኛውም ዜጋ እኔም በዛ እድሜዬ ከእነሱ ጋር ማውራት መተያየት መቻሌ እንዳለ ሆኖ ከዛ በላይ ግን ብዙ አይነት እውቀቶችን ያገኘሁበት ወቅት ነበር፤ አብሬያቸው ፈረንሳይኛ ቋንቋ ተምሬያለሁ፤ በየሳምንቱ ትምህርታዊ ጽሁፎች እየተዘጋጁ በየሙያቸው ገለጻ ሲደረግ ተከታትያለሁ፤ በዚህም ለሕይወቴም ትልቅ ትምህርት የሚሆነኝን ስንቅ አግኝቻለሁ" ይላሉ።

ከሶስት ዓመት ቆይታ በኋላ ይህ ማቆያ ተዘጋና ባለስልጣናቱም ወደማዕከላዊና ከርቸሌ ሄዱ። በዚህ ወቅት የባለስልጣናቱ ጥያቄ ዶክተር ይልቃል አብሮን ይዘዋወር የሚል ነገር ፤ እሳቸው ግን ከፍ ያለ የትምህርት ፍላጎት ስለነበራቸው ቢጠየቁም ፍቃደኛ አልሆኑም ፤ በአንጻሩ ሆስፒታል መግባት እንደሚፈልጉና ከእነሱ ጋር እንደማይሄዱ አሳወቁ። በዚህም ራስ ደስታ ሆስፒታል ተመደቡ። ለአንድ አመት ተኩል ሙያዊ አገልግሎታቸውን ከሰጡ በኋላ የድረ ምረቃ ትምህርታቸውን ለመከታተል ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አቀኑ።

ፕሮፌሰር ይልቃል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህክምና ትምህርት ቤት ምርጫቸው የዓይን ህክምና አደረጉ። ለዚህ ደግሞ ዋናው ምክንያታቸው ገጠር ላይ ያሉ በዓይን ህመም የሚሰቃዩ ሰዎች ነበሩ። ችግሩን ለመቅረፍም የዓይን ሐኪም መሆንን ተቀዳሚ ምርጫቸው አደረጉ።

".....በእኛ አካባቢ ሰዎች በዓይን ህመም ምክንያት ብዙ ሲቸገሩ አይ ነበር። በተለይ የዓይን ማዝ (ትራኩማ) የሚባለው በሽታ የብዙዎችን ዓይን አጥፍቷል። በተለምዶ ፀጉር በቀለ በሚል የሰዎች የዓይን እይታ ሲጠፋም አይ ነበር። ይህንን ለመቅረፍ ደግሞ የዓይን ሐኪም መሆን አስፈላጊ ሆኖ ይሰማኝ ነበር" ይላሉ የዓይን ህክምና ትምህርት ክፍል የገቡበትን ምክንያት ሲያስረዱ።

በመጀመሪያም ፈልገው የተቸገረ ወገናቸውን እረዳበታለሁ ብለው የጀመሩት የዓይን ህክምና ትምህርት ከገቡበት በኋላ እጅግ ወደዱት። ፕሮፌሰር ደግሞ በባህርያቸው ረጋ ያሉ ለሚያደርጉት ነገር ጥንቃቄን የሚያስቀድሙ መሆናቸው በጣም ስስ የሆነውንና ከፍ ያለ ጥንቃቄን የሚፈልገውን ዓይንን ለማከም ትክክለኛው ሰው ሆኑ።

".....የዓይን ህክምና ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄን የሚጠይቅ ነው ፤ እኔ ጊዜ ወስጄ በምፈልገው መንገድ ጥንቃቄ አድርጌ በቻልኩት መጠን ለመስራት ነው የምሞክረው ከዚህ አንጻር ደግሞ ባህርዬም ረድቶኛል መሰለኝ እስከ አሁን በስራዬ በጣም ደስተኛ ነኝ" ይላሉ።

ለብዙ ዓመታት በተወለዱበት ወረዳ ላይ ብቸኛው የሕክምና ዶክተር ሆነው የዘለቁት ፕሮፌሰር ይልቃል፤ በዚህም ምክንያት ቤተሰቦቻቸውን ለማየት በሄዱበት አጋጣሚም ሆነ በሌላ ጊዜ የአካባቢውን ህብረተሰብ በሙያቸው ሳያገለግሉ ተመልሰው አያውቁም። የዓይን ሐኪም ከሆኑ በኋላም ቢሆን ያላቸውን እውቀት እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን ጭነው በመሄድ ለብዙዎች መፍትሔ ሰጥተው ነው የሚመለሱት።

ፕሮፌሰር የሰብ ስፔሻሊቲ ትምህርታቸውን አሜሪካን አገር ነው የተማሩት ፤ እዛ በትምህርት ላይ ሳሉም ወዲያው ጨርሰው አገራቸው መመለስን ነበር የሚያስቡት ምክንያቱም እዚህ ብዙ የእሳቸውን ህክምና የሚፈልግ የአገራቸው ልጆች እንዳሉ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ።

"....አሜሪካን አገር ለትምህርት ስሄድ ገና ወጣት ነበርኩ፤ አላገባሁም ምንም ወደኋላ የሚያስቀረኝም ነገር አልነበረም፤ ግን እዛ ቀርቼ ከማገኘው የኢኮኖሚ ጥቅም ይልቅ እውቀቴን ይዤ አገሬ ብገባ ምን ያህል ዜጎችን እንደማገለግል ለአገሬም አልኝታ እንደምሆን አውቅ ነበር በመሆኑም ብዙ ሰዎች እንድቀርና ጥሩ ሕይወት እንዲኖረኝ ቢያግባቡኝም እኔ ግን አልፈለኩምና ትምህርቴን እንዳጠናቀቅሁ ወደአገሬ ነው የገባሁት" ይላሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ ይላሉ ፕሮፌሰር " ...ከዚህ ስሄድ ትልቅ ሃላፊነት ይዤ ነው የሄድኩት ፤ ተመልሼ ካልመጣሁ መታከም የማይችሉ በሽተኞች ነበሩኝ፤ እንዲሁም እኔ የተላኩት እውቀት ይዤ መጥቼ እንዳስተምር ፣ እንዳክም ነው ተከፍሎልኝ ነው የተማርኩት፤ በመሆኑም ይህንን ውለታ መብላት አልፈለኩም። ከምንም በላይ ደግሞ እዛ ብቀር ለገንዘብ ነው የእኔን አገልግሎት የአሜሪካን ህዝብ ይፍልጋል ማለት አይቻልም፤ የአገሬ ስዎች ግን ከምንም በላይ አስፈልጋቸዋለሁ ብዙ አገልግሎቴን የሚሹ አሉ ለአገሬም ጥሪት ነኝ" ይላሉ።

"....አሁን በአገራችን የዓይን ህክምና አሰጣጥ ላይ የሚታዩ እድገቶችና ለውጦች ሰፊ ናቸው። ከዚህ ቀደም አገር ውስጥ የማይሰጡ ህክምናዎች አሁን በራሳችን ባለሙያዎች መሰራት ጀምረዋል። ለዓይን ህክምና ጆሮ መሰጠት ተጀምሯል። ይህም ህክምና እንዲያድግ እያደረገው ከመሆኑም በላይ አሁን ባለንበት ሁኔታም ህክምናው መነቃቃትና መሻሻል ይታይበታል የዓይን ሐኪሞችም በቁጥርም በምንሰጠው አገልግሎትም እየበዛን ነው"ይላሉ።

በአገራችን ከፍተኛ ቁጥር ያለው የዓይን ሐኪም ያለው ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ነው። ይህ የዓይን ትምህርት ክፍል ደግሞ የድረ ምረቃ ትምህርት መስጠት ከጀመረ 42 ዓመት ሆኖታል። እዚያ ያለን ብዙዎቻችን ብዙ ልምድ አካብተናል፤ ውጭ አገር ሄደን ተምረናል፤ ከዚህ ቀደም በአገር ውስጥ ሲሰሩ ያልነበሩ የቀዶ ህክምና ስራዎች እንዲጀመሩ የራሳችንን አስተዋጽኦ አድርገናል ይላሉ።

ፕሮፌሰር ይልቃል እንዳሉትም እሳቸው ብቻ እንኳን በሰብ ስፔሻሊቲ (ኦኩሎፕላስቲክስ) ሙያ ማለትም ዓይን አካባቢ መበላሸት፣ ለምሳሌ የዓይን ሽፋሽፍት መታጠፍ፣ የእንባ ቧንቧ መዘጋት፣ ዓይን አካባቢ ማሳመር፣ እጢዎች ከዓይን ጀርባ፣ ጎንም ሆነ ፊት ለፊት ቢወጡ በቀዶ ህክምን ማስተካከል ላይ የመጀመሪያው ሰው በመሆን በብቸኝነት በርካታ ዓመታትን አገልግለዋል።

የመጀመሪያም እንደመሆናቸው መጠን ሙያው እንዲስፋፋ ሌሎች ባለሙያዎችም በዘርፉ እንዲሰሩ ችግሩ ያለባቸውም ሰዎች አገልግሎቱን እንዲያገኙ ላቅ ያለ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። አሁን ላይም በዘርፉ ከሰባት ያላነሱ ባለሙያዎች ሊኖሩ ችለዋል። በቀጣይ ደግሞ ትምህርቱን በአገር ውስጥ ለመስጠት ዝግጅትም በማድረግ ላይ ናቸው።

ዳግማዊ ምኒልክ ውስጥ እሳቸውን ጨምሮ ከሳቸውም በፊት የነበሩ እንደውም የእሳቸውም መምህራን ሁሉ በሙያቸው ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ብዙ ዜጎች ውጭ አገር እየሄዱ ይታከሙ የነበሩትን በማስቀረት አገር ውስጥ ታክመው እንዲድኑም አስችለዋል።

በዓይን ህክምና ሕይወት ላይጠፋ ይችላል ነገር ግን ለዓይን ሐኪም ዓይን መጥፋትም እንደ ሕይወት መጥፋት ነውና በዚህ ልክ ያዘኑበት ጊዜ ነበር? ፕሮፌሰር ".....እስከ አሁን የሰራኋቸው ስራዎች ሁሉ የተሳኩ ነበሩ ማለት አይደለም፤ ያልጠበቅነው ነገርም ሊያጋጥም ይችላል ፤ እንደዚህ አይነት ነገር ሲያጋጥመኝ እንቅልፍ አልተኛም፤ በተቻለ መጠን ወደ ኦፕሬሽን ክፍል ሳልገባ ከታካሚዎች ጋር ቁጭ ብዬ እነጋገራለሁ፤ ከወጡ በኋላም እንደዛው፤ ነገር ግን ለማከም ጥረት በሚደርግበት ጊዜ የሚያጋጥም ችግር ያለ ነው መጽሐፍ ላይም ተጽፏል፤ አንዳንዱ ጉዳት ደግሞ ምንም ሊደረግለት የማይችል የሚሆንበት አጋጣሚም አለ፤ ልቤን ከሚሰብሩት ነገሮች መካከል ግን ዓይን ላይ ወይም ዓይን አካባቢ እጢ ወጥቶ ወደካንሰርነት ተቀይሮ አይኑን አጥፍቶ በጣም ቆስሎ፤ በጣም ሹቶ፤ ትል አፍርቶ የሚመጡ ሰዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች ምናልባትም ሆስፒታል እስከሚደርሱ ረጅም ጊዜ የቆዩት አንድም በግንዛቤ ማነስ ወይም በአቅም ማነስ ወይም በሁለቱም ምክንያት ነው፤ እንዲያውም የድህነታችን መገለጫ ሁሉ ይመስለኛል፤ በመሆኑም እነዚህን ሰዎች የቅድሚያ ቅድሚያ ሰጥቼ ነው ከችግራቸው ለማላቀቅ የምጥረው" በማለት በስራቸው ላይ ስለሚመለከቱት ነገር ይናገራሉ።

አልከደን ብሎ የመጣ አይን እንዲከደን፣ የተከደነው ሲከፈት፣ ወደአንድ በኩል የተጣመመውን ወደቦታው እንዲመለስ ማድረግ ትርፍ ነገር ካለ አንስቶ ማሳመር ፕሮፌሰር ከተካኑባቸው ብሎም ለዓመታት በብቸኝነት ከሰሯቸው የህክምን ስራዎች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው። ሆኖም በዚህ ስራ ሰዎችን እንደሚፈልጉት አድርጎ ማስደሰቱ ለእሳቸውም ደስታ ቢፈጥርላቸውም ያን ያህል ግን አብሮ የሚቆይ ወይም ደግሞ ከባድ የዓይን ችግሮችን ይዘው መጥተው እንደሚሰሩላቸው ሰዎች እርካታ እንደማይፈጥርባቸውም ነው የሚናገሩት።

ፕሮፌሰር ትዳር የመሰረትኩት ቆየት ብዬ ነው ይላሉ፤ ከወራት በኋላም 15 ዓመት የጋብቻ ዘመናትን ያስቆጥራሉ። በእነዚህ ዓመታት ደግሞ ፋርማሲስት ከሆኑት ባለቤታቸው አንድ ወንድና ሁለት ሴት ልጆችን ወልደዋል። ምንም እንኳን ልጆቹ ህጻናት ሆነው መጨረሻቸው የታወቀ ባይሆንም አንዷ" እንደ አባቴ የዓይን አካሚ ነው የምሆነው" ትላለች። ሌላዋ የልብ ሐኪም የመሆን ፍላጎት አላት በማለት የልጆቻቸውን ሁኔታ ይናገራሉ።

መልዕክት

ሁልጊዜ የምናገረው ነገር ነው። ሰው የሚወደውን ስራ ሲሰራ ውጤታማ ይሆናል፤ ነገር ግን ገንዘብ አገኝበታለሁ ብሎ የማያዋጣ የትምህርት መስክ ወይም የስራ መስክ ለመምረጥ ብሎ መሄድ የተሰጠውን መክሊቱ አለማወቅ ነው። በተለይም የህክምና ሙያ ፍቅር የሚጠይቅ በመሆኑ በገንዘብ መተመኑ አዋጭ አይደለም። እኔ እንኳን ዛሬ ላይ ዋጋዬ ስንት እንደሆነ አላውቀውም። የማንንም ዋጋ መተመንም ከባድ ነው። የህክምና ስራ ማለት እንደማንኛውም የቢሮ ስራ ተጥሎ የሚወጣ ነገ እጨርሰዋለሁ የሚባል አይደለም፤ አብሮ ቤት ድረስ የሚሄድ፤ ዛሬ እረፍት ላይ ነኝ አልሰራም፤ ተኝቻለሁ አልቀሰቀስም፤ ማለት የማያስችል ነው።

በመሆኑም ሐኪም የራሱን ምቾት እያሰበ ህክምና እሰራለሁ ካለ አይሆንም፤ በመሆኑም ለስራው እራስን ያለምንም ስሌት መስጠት ይጠይቃል። ወጣቶች ማንኛውም ሙያ ላይ ሲሰማሩ ስራን ለአለቃ ወይንም ለገንዘብ ሳይሆን ለህሊናቸውና ለፈጣሪያቸው ታማኝ በመሆን መስራት ከቻሉ ስኬት ላይ የማይደርሱበት ምንም ምክንያት አይኖርም።

የበጎ ፈቃድ ስራዎች

ፕሮፌሰር ከማከም ከማስተማር ባለፈ በተለያዩ የበጎ አድራጎት ስራዎች ላይ ይሳተፋሉ። ከዚህም መካከል በትውልድ መንደራቸው ጤና ጣቢያ እንዲቋቋም ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፤ ሁለተኛ ደረጃና የመሰናዶ ትምህርት ቤት እንዲከፈት ጓደኞቻቸውንና የተለያዩ በጎ አድራጊዎችን በማስተባበር ሰርተዋል። ቤተ መጽሐፍት አሰርተዋል፤ ቴክኒክና ሙያ አካባቢው ላይ እንዲኖር የራሳቸውን ድርሻ አበርክተዋል።

በሌላ በኩልም ጸረ-ወባ ማህበርን ከመሰረቱት ኢትዮጵያውያን አንዱ ናቸው፤ በአገር አቀፍ ደረጃም በተለያዩ ኮሚቴዎች ማለትም በጤና ሚኒስቴር የዓይነ ስውርነት መከላከል ኮሚቴ አባል ናቸው፤ በዳካ ናሽናል ድራግ አድቫይዘሪ ኮሚቴ ላይም ለረጅም ዓመታት አባል ሆነው ሰርተዋል። የኢትዮጵያ የጥራት ሽልማት ድርጅትም የዳኞች ኮሚቴ አባል ሆነው ያገለግላሉ። በተጨማሪም ፕሮፌሰር ይልቃል በአገር ውስጥና በውጭ አገር በሙያቸው በአማካሪነት ይሰራሉ፡፡

ኢኮኖሚ

ባህልና ቱሪዝም

የቱሪዝም አገልግሎት ዘርፍን ለማዘመን- ጠቋሚ አቅጣጫዎች

ዳግም ከበደ

የኢትዮጵያ መንግስት የቱሪዝም ዘርፍን ከማህበራዊ ጉዳይ አውጥቶ ወሳኝ ወደሆነው ቁልፍ ኢኮኖሚያዊ ግቦችን ማሳካት ከሚችሉ ግንባር ቀደም ዘርፎች ውስጥ አካቶታል። በዚህም የቱሪዝም ልማት፣ ፕሮሞሽንና መሰል ጉዳዮችን በትኩረት በመስራት ከዘርፉ የሚገኘውን የላቀ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማስጠበቅ እንደሚሰራ ግልፅ አድርጓል። ለዚህ እቅድ መሳካት ወሳኝ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል ደግሞ የዘርፉን የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ማዘመን አንዱና ዋነኛው ነው።

በቱሪዝም ዘርፍ ላይ ሙያቸውን ያዳበሩ ምሁራን "ቱሪዝም ከአንድ ቦታ ወደሌላ ስፍራ የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው" ይላሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ ጉዞውን የሚያደርገው ግለሰብም ይሁን ቡድን ከቋሚ መኖሪያው ለአጭር ጊዜ አሊያም ረዘም ላለ ቆይታ ይንቀሳቀሳል ማለት ነው። ከዚህ ውስጥ ደግሞ የመስህብ ስፍራን ለመመልከት እንዲሁም ታሪካዊ፣ ተፈጥሯዊና የዓለም ቅርስ መገኛዎችን ለመጎብኘት የሚደረገው ጉዞ በዋነኝነት ይጠቀሳል። ይህ ደግሞ በመዳረሻው ለሚገኘው አገር፣ ዜጎች እንዲሁም በአገልግሎት ዘርፍ ላይ ለተሰማሩ አካላት ኢኮኖሚያዊ አቅምን የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ የአገር ገፅታን ለመገንባት ጠቀሜታ እንደሚኖረው ያብራራሉ።

በዚህ ሂደት ውስጥ የተሟላና አርኪ የአገልግሎት ዘርፍ ያላቸው፣ ብቁ ባለሙያና ስነ ምግባርን (የአገልጋይነት ባህሪ) የተላበሰ የሰው ኃይልና ዘመናዊ አሰራር የዘረጉ አገራት ጎብኚዎች ቆይታቸውን አራዝመው ገንዘባቸውን በበቂ ሁኔታ አውጥተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ እድሉን ይከፍታሉ። በዚህም ምጣኔ ሃብታቸው እንዲያድግና ዜጎቻቸው በሚፈጠረው የስራ እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋሉ።

ኢትዮጵያም ከዚህ መሰል እድል ተጠቃሚ ለመሆንና የቱሪዝም ዘርፉን ግንባር ቀደም ዘርፍ አድርጋ አስቀምጣለች። በተለይ የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ አንዱና ዋንኛው ግብ በዚህ ዘርፍ ላይ የሚያጠነጥን ነው። ከሰነዱ መረዳት እንደምንችለው ቱሪዝምን ተወዳዳሪ ለማድረግ የዲጂታል አሰራር መዘርጋት ያስፈልጋል። ይህንን ለማድረግ ሶስት መልካም አጋጣሚዎች መለየታቸውንም ያመለክታል። የመጀመሪያው የቱሪዝም ዲጂታላይዘሽን ግብረ ኃይል በማቋቋም የቱሪዝም ኢንዱስትሪውን ዲጂታላይዝ ማድረግ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የዲጂታል የገበያ ስርዓትን በማበጀት የቱሪስት ፍሰትን እና የቆይታ እና ተሳትፎ መጠኑን ማሻሻል ነው፡፡ ሶስተኛው ደግሞ በቱሪዝም ዘርፍ የተሰማሩ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የዲጂታል አገልግሎት እንዲሰጡ አቅም መገንባት ነው፡፡

ይህ የሚያመለክተን ዘመኑን የዋጀ የቱሪዝም አገልግሎት ዘርፍ ለመዘርጋት ስልት መነደፉን ሲሆን፣ ወደዚያ ግብ ለመድረስ ደግሞ አያሌ ተግባራት ከፊት ለፊታችን እንደሚገኙ ነው። ለመሆኑ የአገልግሎት ዘርፉን አዘምኖ፣ ከከፍተኛ የቱሪስት ፍሰት የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ አቅም አሳድጎና ቱሪስቶች የቆይታ ጊዜያቸውን አራዝመው ፈሰስ እንዲያደርጉ የሚያስችል ምን ስልት መከተል ይኖርብናል? ለሚለው ጥያቄ የዝግጅት ክፍላችን በቅርቡ በቱሪዝም ዘርፉ ላይ በተካሄደ አንድ መድረክ ላይ የመወያያ ፅሁፍ ያቀረቡ የሆቴልና ቱሪዝም ኢንስቲቱዩት የቱሪዝም ባለሙያና መምህር የአቶ ማሩ እማኙን ሃሳብ ከዚህ እንደሚከተለው ያቀርባል።

አቶ ማሩ የዓለም የቱሪዝም ድርጅት (ደብሊው ቲኦ) "ቱሪዝም የሰዎች እንቅስቃሴ ነው" በሚል ቱሪዝምን ይተረጉመዋል በማለት ስለ አገልግሎት አሰጣጥና መሰል የቱሪዝም ፅንሰ ሃሳቦች ከመግባታችን አስቀድመን በቅጡ ትርጉሙን ልንረዳው ይገባል በማለት ያስረዱናል። በዚህ ሂደት ውስጥ ጎብኚዎች ከተለመደው ስፍራቸው አዲስ ወደሆነው ሲንቀሳቀሱ የተለያዩ ልምዶችንና መዝናናቶችን እንደሚሹ ይናገራሉ። በዚህ ሂደት ላይ አገልግሎት

ኢትዮጵያ የቱሪስቶችን ቆይታ የሚጨምሩ እንደ ወዳጅነት ፓርክ አይነት አዳዲስ ፓርኮች ባስቤት ሆናለች ፤ መረጃውን ለቱሪስቶች ማድረስ ላይ ግን ብዙ ሲሰራ ይገባል

ዘርፉ እንደሚገባና ከጎብኚዎች አሊያም ቱሪስቶች ጋር መስተጋብር የሚፈጥር እንደሆነ ይናገራሉ።

"ጎብኚዎች ከአካባቢያቸው ራቅ ያለ ቦታ ሲጓዙ የሚጠብቁትና የሚፈልጉት የአገልግሎት አይነት አለ" የሚሉት አቶ ማሩ፣ ይህንን ፍላጎታቸውን በተገቢው መንገድ የምንሰጣቸው ከሆነ ደስተኞችና ቆይታቸውን የማራዘም ፍላጎት አሊያም ደግሞ በድጋሚ የመምጣት፤ ከዚያም አለፍ ሲል ወደመጡበት ስፍራ ሲመለሱ መልካም ገፅታን ለመገንባት ፍቃደኛ እንደሚሆኑ ያመለክታሉ። በዚህ ምክንያት የአገልግሎት ዘርፎቹ አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ እንደሚገባቸው ይመክራሉ።

እንደ አቶ ማሩ ገለጻ፤ ቱሪስቶች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ቆይታቸውን አጠናቀው በሚመለሱበት ጊዜ በፎቶ፣ በተንቀሳቃሽ ምስል እንዲሁም ትውስታቸውን ይዘው ይመለሳሉ፤ ለኢትዮጵያም ሆነ በውስጧ ለሚኖሩት ዜጎች ጎብኚዎች መልካም ስምና አድናቆትን ይዘው እንዲመለሱ አገልግሎት ዘርፉ የበኩሉን ድርሻ መወጣት ይኖርበታል።

በተለይ ቱሪዝም ሲታሰብ መሰረታዊና ግንባር ቀደም የአገልግሎት ዘርፍ የሆነው አንዱ "የትራንስፖርት ዘርፍ" መሆኑን የሚጠቅሱት አቶ ማሩ፣ በዚህ ዙሪያ ራሱን የቻለ የተደራጀ ነገር መኖር እንዳለበት ይገልፃሉ። ሌላው ጎብኚዎች ስለሚገኙበት አንድ መዳረሻ ስፍራ ራሱን የቻለ ምስል ከሳችና እውቀትን የሚያስጨብጥ የተቀናጀና የተናበበ አሰራር ሊኖር እንደሚገባም ይጠቁማሉ። ይህ እንዲሆን አገልግሎት ሰጪዎች ወጥ አሰራር ሊኖራቸው እንደሚገባ ይናገራሉ። ለምሳሌ ያህልም አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ ታሪካዊ፣ ተፈጥሯዊ፣ ሰው ሰራሽና ሌሎች ቅርሶችን በተመለከተ ጎብኚዎች ተመሳሳይ መረጃን ማግኘት እንደሚገባቸውን ነው በምክረ ሃሳባቸው ላይ የሚያነሱት።

"ቱሪስቶች ረጅም ቆይታ ሳያደርጉ መዳረሻቸው ሌላ አገር ሆኖ ትራንዚት ሲያደርጉ ለአጭር ጊዜ ቆይታ ጉብኝት ሊያደርጉ ይችላሉ" የሚሉት የቱሪዝም ባለሙያውና መምህሩ፣ በተለይ አዲስ አበባን እንደ ትራንዚት ሊጠቀሙ የሚችሉ በርካታ ቱሪስቶች መኖራቸውን ነው የሚያመለክቱት። በዚህ ጊዜ የሚኖራቸውን ከ6 እስከ 72 ሰዓት የሚደርስ የአጭር ጊዜ ቆይታ በተጨናነቀ ኤርፖርት ወይም አልጋ ክፍል ውስጥ ከሚያሳልፉ በዋና ከተማዋ የሚገኙ የቱሪዝም መዳረሻ ስፍራዎች ላይ እንዲያደርጉ የሚያበረታታቸው ልዩ ልዩ የአገልግሎት አማራጮች መኖር እንዳለባቸውም ይመክራሉ።

በአሁኑ ወቅት መንግስት በአዲስ አበባ የጀመራቸውና ሰርቶ ያጠናቀቃቸው ሜጋ የቱሪዝም መዳረሻ ስፍራዎችን በቀላሉ እንዲመለከቱ እድሉን ማመቻቸት እንደሚያስፈልግ ነው የሚገልፁት። ይህን ለማድረግ ምቹ የትራንስፖርት አማራጭና የተደራጀ መረጃን ማሰናዳት እንደሚገባ ይናገራሉ። ይህን ማድረግ ከተቻለ ትራንዚት የሚያደርጉት ቱሪስቶች ዶላራቸውን አውጥተው እንዲሄዱ ጥሩ መንገድ ይከፍታል ይላሉ።

"ቱሪዝም በዋናነት እና በመጨረሻ ዋና ግብነት የሚያስቀምጠው ዘርፉን ተጠቅሞ እንዴት ለዜጎች የስራ እድል መፍጠር ይቻላል የሚል ፅንሰ ሃሳብ ላይ የሚያጠነጥን ነው" የሚሉት መምህሩ፤ ቀደም ሲል ዘርፉ በማህበራዊ ዘርፍ ላይ የተካተተ እንደነበር ያስታውሳሉ፤ አሁን ግን ከስራ ፈጠራና ከሚያበረክተው ምጣኔ ሃብታዊ አስተዋጽኦ አንፃር ተቃኝቶ ወደ ኢኮኖሚ ዘርፍ እንደተካተተ ይናገራሉ። በዋነኝነት ግን ሰፊ የስራ እድል መፍጠሩ በመንግስት ቁልፍ የኢኮኖሚ ዘርፎች ውስጥ እንዲገባ እንዳስቻለው ነው የሚያስረዱት። በዋናነት በዘርፉ የስራ እድል ፈጥሮ ስኬታማ የአገልግሎት ዘርፍ እንዲኖር ለማስቻል እንደሚሰራ ይጠቁማሉ። ታዲያ ይህንን እድል በሚገባ መጠቀምና በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ክፍሎች የሚገኙ መዳረሻ ስፍራዎችን በተገቢው ተገንዝቦ ወደ እድል መቀየር እንደሚያስፈልግ ያሳስባሉ።

"ቱሪዝም ሲታሰብ ሶስት መሰረታዊ ነገሮች አሉ" የሚሉት መምህር ማሩ፣ አንደኛው መስህቡና መዳረሻ ስፍራው መኖሩ ሲሆን፣ ሁለተኛውና ትልቁ ነገር ወደዚያ ሰፍራ ለመሄድ የሚያስችል የተመቻቸ የትራንስፖርት አማራጭ መኖር ነው ይላሉ። ሶስተኛው ደግሞ የተለያዩ የምግብ፣ የመዝናኛ እንዲሁም ልዩ ልዩ የግብይትና የአገልግሎት መስጫ ስፍራዎች መኖር መሆኑን ይጠቁማሉ።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ እነዚህ ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች ሲሟሉና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት ሲችሉ ቱሪስቱ በሚፈልገው አግባብ መስተናገድ ይችላል። የአገልግሎት ዘርፉ ጥራትና ውጤታማነትም የጎብኚውን የመቆየት እና ጉብኝቱን የማራዘም ፍላጎቱን በእጅጉ ይጨምረዋል። ይህ ሲሆን የተሻለ የገንዘብ ፍሰት ከመፍጠር ባለፈ ሰፊ የስራ እድልም ይፈጠራል።

እንደ መውጫ

በርካታ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፤ ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ አገር ነች። ኢትዮጵያ ከ3 ሚሊዮን ዓመታት በላይ እድሜ ያስቆጠረው "የሉሲ" ወይም ድንቅነሽ አፅም መገኛ ናት፡፡ የአረቢካ ቡና ዝርያ መገኛም ነች። የዓለማችን ረጅሙ ወንዝ ጥቁር አባይም የሚገኘው በኢትዮጵያ ነው። የኤርታሌ የእሳተ ገሞራ ሐይቅና የዓለማችን እጅግ ረባዳና ሞቃት ስፍራ ዳሎልም የሚገኙት በኢትዮጵያ ነው። ይህ ብቻ አይደለም። ኢትዮጵያ የንግስት ሳባ አገር ነች፣ የሙሴ ጽላትም በኢትዮጵያ ይገኛል ተብሎ ይታመናል፤ በአክሱም ፅዮን ቤተክርስቲያን። ከእነዚህ ሌላ ለመዝናናት አመቺ የሆኑ በርካታ የስምጥ ሸለቆ ሐይቆችና ፍል ውኃዎች፣ እንዲሁም የዱር እንስሳት ፓርኮችና መጠበቂያዎች ይገኛሉ።

ኢትዮጵያ በርካታ ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊ፤ ሰው ሰራሽና ባህላዊ ቅርሶችን በዩኔስኮ በማስመዝገብ በአፍሪካ ቀዳሚዋ አገር ለመሆን በቅታለች። በተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች የበለፀጉች፤ የቱሪስት መስህብ ያላትና እነዚህንም ቅርሶች በዩኔስኮ መዝገብ በብዛት በማስመዝገብ ከአፍሪካ አገራት ቀዳሚዋ ብትሆንም፣ የአገሪቱ የቱሪዝም ዘርፍ ግን የሚፈለገውን ያህል ወይም የሚገባውን ያህል አላደገም።

ለዚህ እንደ ዋንኛ ምክንያት የሚጠቀሰው ዛሬ በስፋት ያነሳነው የአገልግሎት ዘርፉ በተገቢው አለመዘመን ሲሆን፣ በልዩ ልዩ የቱሪዝም ዘርፉ ተሰማርተው የሚገኙት አገልግሎት ሰጪዎች የስነ ምግባር፣ የእውቀትና መሰል ቱሪስቱ የሚፈልገው የአገልጋይነት ባህሪያት መላበስ ባለመቻላቸው እንደሆነ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ መንግስት የቱሪዝም ዘርፉ የኢትዮጵያ የጀርባ አጥንት እንደሆነ በማመን ልዩ ትኩረት መስጠቱን ነግሮናል። በተግባር ሰፋፊ ልማቶችን፣ ፕሮጀክቶችን እያከናወነ መሆኑን የሚያመላክቱ መረጃዎችን መጥቀስ ይቻላል። ይሄን መልካም አጋጣሚ መጠቀም ከምንም ነገር በላይ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል። በተለይ በግሉ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሃብቶች በቱሪዝም ሆስፒታሊቲ ዘርፍ፣ በፕሮሞሽንና የገበያ ልማት ብሎም በአስጎብኚ ድርጅቶች ውስጥ በቀጥታ ሊሳተፉ ይገባል። የዚህ ድምር ውጤት ደግሞ "ምድረ ቀደምት" አገራችንን ለመላው ዓለም ከፍ አድርጎ ማስተዋወቅ እንዲቻል ከማድረጉም ባለፈ ኢኮኖሚያዊ ትርፉ ለአገር እድገት ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት ጥርጥር አይኖረውም።

ስፖርት እና መዝናኛ

ሳምንቱን በታሪክ

የመጀመሪያው የተጻፈ ሕገ መንግሥት

ዋስልኝ አየሁ

ኢትዮጵያ እንደ ብዙዎቹ የአውሮፓና ሌሎች ዓለም አገራት በንጉሣዊ ሥርዓት ስትተዳደር የኖረች አገር ናት። በእነዚህ ንጉሣዊ ሥርዓቶች የነበረው አስተዳደር ብዙውን ዘመን በተጻፈ ዘመናዊ ሕገ መንግሥት አልነበረም።

ሆኖም ግን ኢትዮጵያ የተጻፈ ዘመናዊ ሕገ መንግሥት የጀመረችውም በዚያው በንጉሣዊ ሥርዓቱ ዘመን ነው። ምንም እንኳን ከሥርዓት ለውጥ በኋላ የሚመጣው መንግሥት ቢቀያይራቸውም የመጀመሪያውን የተጻፈ ሕገ መንግሥት የጀመረችው ግን በንጉሳዊ ሥርዓቱ ዘመን ነው።

በዛሬው ሳምንቱ በታሪክ ዓምዳችን በዚህ ሳምንት የጸደቀውንና በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ዘመናዊ የተጻፈ ሕገ መንግሥት፤ በአምቦ ዩኒቨርሲቲ የህግ ባለሙያ የሆኑት ሚኪያስ በቀለ በአዲስ ማለዳ ጋዜጣ የጻፉትን፣ የታሪክ ጸሐፊው ፍስሐ ያዜ «የኢትዮጵያ የአምስት ሺህ ዘመን ታሪክ ቅጽ 2» መጽሐፍ እና ከልዩ ልዩ ድረ ገጾች ያገኘናቸውን መረጃዎች ዋቢ አድርገን እናስታውሳለን።

ንጉሰ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን ዘመናዊ (የተፃፈ) ሕገ መንግሥት ያጸደቁት ከ91 ዓመታት በፊት ሐምሌ 9 ቀን 1923 ዓ.ም ነው።

ሕገ መንግሥቱ ሲጸድቅ ንጉሱ የተናገሩትን የፍስሐ ያዜ መጽሐፍ እንዲህ ይነግረናል።

«...ሕግ ለሰው ከሁሉ የበለጠ የሚጠቅም መሆኑን ማንም አይስተውም። መከበርም መጠቀምም የሚገኙት በሕግ መተካከል የተነሳ ነው። መዋረድም መጎዳትም የሚመጡት በሕግ መጓደል የተነሳ ነው። ግፍ እና በደልም የሚበዙት ሕግ ባለመቆሙ ነው....»።

በንጉሣዊ ሥርዓቱ ዘመን በሕይወት የነበሩ አባቶች ሲያወሩ እንደምንሰማው በዘመኑ «በሕግ አምላክ!» የሚባል ነበር። «በሕግ አምላክ!» ከተባለ ምንም ዝንፍ አይልም። ወደታች የሚወርድ የወንዝ ውሃ «በሕግ አምላክ!» ሲባል ይቆማል ይላሉ አባቶች። አባባሉ ግነት እንዳለው ግልጽ ነው፤ ዳሩ ግን የሕግን ሃያልነት ለመግለጽ የተጠቀሙት ነው። በዚህ እሳቤ ውስጥ ነው የመጀመሪያው ዘመናዊ የተጻፈ ሕገ መንግሥት የጸደቀው።

የፍስሐ ያዜ መጽሐፍ እንደሚነግረን፤ ሕገ መንግሥቱ ከመጽደቁ በፊት በመሳፍንቱ እና በመኳንንቱ መካከል ከፍተኛ ክርክር ነበር። ጠቅለል ሲደረግ፤ የመሳፍንቱ ሀሳብ ኢትዮጵያ በአውራጃ ተከፋፍላ የመሳፍንቱ የበላይነት እንዲቀጥል ነው። ሥልጣንም ለልጅ ልጆቻቸው እንዲተላለፍ ነው፤ ዳሩ ግን ወንጀል ሰርተው ከተገኙ ክርስታቸው እንዲነቀሉ የሚል ነው።

የመኳንንቱ ሀሳብ ደግሞ፤ በአጭሩ ሹመት በዘር መሆን የለበትም የሚል ነው። ንጉሱም አስታራቂ ሀሳብ ሰጥተው መሳፍንቱንም መኳንንቱንም ያካተተ እንዲሆን ተደረገ። በንጉሰ ነገሥቱ ይሁንታ ማንም ሊሾም እንደሚችል ተነገረ። በዚህ መንገድ ሕገ መንግሥቱ ሲጸድቅ መሳፍንቱ፣ መኳንንቱና ሚኒስትሮች አብረው ሆነው ነው።

የሕግ ምሁሩ ሚኪያስ በቀለ ጥናታዊ ጽሑፍ ደግሞ ስለዚሁ ሕገ መንግሥት የሚከተለውን ይነግረናል።

«... ሕገ መንግሥቱ የተረቀቀው በንጉሡ ቀጥተኛ ትእዛዝ ሲሆን፣ ያረቀቁትም በሩስያ የተማሩ ተክለሐዋርያት ተክለማርያም የሚባሉ ግለሰብ ነበሩ። ደጃዝማች ተክለሐዋሪያት ሕገ መንግሥቱን ለማርቀቅ አጼ ኃይለሥላሴ በቀጥታ ጥያቄ እንዳቀረቡላቸው፣ ውይይታቸውን በማካተት ስለ ግለ ሕይወት ታሪካቸውን በጻፉት መጽሐፍ ላይ አስፍረዋል...»።

ንጉሡ ሕገ መንግሥቱን ለማስረቀቅ እና ለማውጣት ምክንያት የሆናቸው አገሪቷ ተራማጅ እና ሥልጡን መሆኗን ለዓለም ለማስተዋወቅ ነው። የሚኪያስ በቀለ ጥናት ተከታዮቹን መረጃዎችም ይነግረናል።

ደጃዝማች ተክለሐዋሪያት ሕገ መንግሥቱን ከጃፓኑ (የመጂ ስርወ መንግሥት) ሕገ መንግሥት ላይ በመገልበጥ ቢያረቁትም፤ ከሚንስትሮች እና የክፍለ አገር መኳንንቶች የተውጣጣ 11 አባላት ያሉት የሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚቴ ተቋቁሞ ነበር። ኮሚቴው የእንግሊዝና የጃፓን ሕገ መንግሥቶች ተተርጉመው ቀርበውለት ተወያይቶበት እንደነበርና በቀጥታ ወደ ንጉሡ ተልኮ ነው የጸደቀ።

ንጉሡ ሕገ መንግሥቱን ከማጽደቃቸው በፊት ብላቴንጌታ ሕሩይ እና ራስ ካሳ ከሚባሉ አማካሪዎቻቸው ጋር መክረዋል። ሕዝብ አልተወያየበትም በሚል የሕገ መንግሥቱ ሰነድ ከንጉሡ ለሕዝብ የተሰጠ ስጦታ ተደርጎም ይቆጠራል።

ይህ በኢትዮጵያ የመጀመሪያዊ ዘመናዊ የተጻፈ ሕገ መንግሥት ንጉሡን ሲያስተች የቆየ ነው። በዚያ ንጉሳዊ ዘመን ቢያንስ የተጻፈ ሕገ መንግሥት ማስጀመራቸው ያስመሰግናቸዋል እንጂ ይዘቱ ግን ለንጉሡ ያደላ ነበር። እነዚህ አንቀጾች እንጠቃቅስ።

አንቀጽ ሁለት፡- የኢትዮጵያ መሬትም፣ ሕዝብም፣ ሕጉም በጠቅላላው የንጉሠ ነገሥት ነው

አንቀጽ ሦስት፡- የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከኢየሩሳሌም ንጉሥ ከሰለሞን እና ንግሥት ሳባ ከተባለችው ኢትዮጵያዊ ንግሥት ከተወለደው ከቀዳማዊ ምኒልክ ነገድ ተያይዞ ከመጣው ከንጉሥ ሳህለሥላሴ ዘር ከተወለደው ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እንዳይወጣ በሕግ ተወስኗል።

አንቀጽ አምስት፡- ንጉሰ ነገሥቱ የነጋሲ ዘር በመሆኑና ቅብዓ መንግሥት በመቀባቱ ክብሩ የማይቀነስ፣ ማዕረጉ የማይገሰስ ኃይሉ የማይደፈር ሆኖ በቆየውም ልማድ በአዲሱም ሕግ በሚገባው ሁሉ ይከበራል። ክብሩንም ለመንካት በድፍረት የተነሳ ሰው በሕግ እንዲቀጣ ተወስኗል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት አንቀጾች ንጉሱን በሕግ ባለሙያዎች እነሆ ዛሬ ድረስ ተወቃሽ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። በታሪክ ጸሐፊዎች ግን የዘመኑ እና የሥርዓቱ ባህሪ ነው የሚል ሙግት አለ። ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ለሺህ ዘመናት የኖረ ንጉሣዊና ልማዳዊ ሥርዓትን ነው አዲስ መንገድ ያስጀመሩት፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጻፈ ሕግ እንዲኖረው ያደረጉት... የሚሉ አሉ።

ያም ሆነ ይህ የመጀመሪያው የተጻፈ ሕገ መንግሥት የቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ነው። ለዛሬው የምናስታውሰው የመጀመሪያው የጸደቀበትን ስለሆነ እንጂ እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸውና ሌሎች አንቀጾች ባስነሱት ቅሬታና ሙግት በ1948 ዓ.ም ሕገ መንግሥቱ ተሻሽሏል።

የቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ሕገ መንግሥት ለዘውዳዊ ሥርዓቱ ያደላ ቢሆንም ያመጣቸው ለውጦችም በታሪክ በበጎ ተጽፈውለታል። ለምሳሌ፤ ማንኛውም መሳፍንት እንዳለፈው ዘመን በግሉ ከውጭ አገራት ጋር መጻጻፍ አይችልም። መሳሪያ እና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን በግሉ መቀበል አይችልም። ይህም ሕገ መንግስቱ መሳፍንቱን በቁጥጥሩ ሥር ማድረግ አስችሎታል።

በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ፓርላማ የተመሰረተውም በዚሁ በመጀመሪያው የተጻፈ ሕገ መንግሥት ነበር። ይሄው ሐምሌ 9 ቀን 1923 ዓ.ም የጸደቀው የንጉሡ ሕገ መንግሥት ሁለት ምክር ቤቶችን አቋቁሟል። ምክር ቤቶቹም የሕግ መወሰኛ(ላዕላይ) ምክር ቤት እና የሕግ መምሪያ(ታህታይ) ምክር ቤት የሚባሉት ናቸው።

የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት ንጉሡን ለረዥም ጊዜ ካገለገሉ መኳንንት፣ ሚንስትሮች፣ ዳኞች እና የውትድርና መኮንኖች ውስጥ በቀጥታ በንጉሡ የሚመረጡ ናቸው። አባላቱ የመሳፍንት ዘር ባይሆኑም መንግሥትን ያገለገሉ ከሆነ ከተራ ዜጎችም ይመረጣሉ። ይሄውም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 31 ላይ ተቀምጧል።

የሕግ መምሪያው ምክር ቤት አባላት ደግሞ «ሕዝቡ የራሱን እንደራሴ መምረጥ እስከሚችል ድረስ» በሚል በመኳንንቱ እና በሹመኞች ተመርጠው እንደሚላኩ ሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 32 ይደነግጋል።

አንድ አባል በተመሳሳይ ጊዜ የሁለቱም ምክር ቤቶች አባል መሆን አይችልም። ምክር ቤቶቹ አራት ዓመታት ካገለገሉ በኋላ በአምስት ዓመቱ የፋሽስት ጣልያን ወረራ ጊዜ ሥራቸውን አቁመው ቆይተው በድጋሚ ሥራቸውን የጀመሩት በ1933 ዓ.ም መሆኑን አቶ ቃልአብ ታደሰ ስለ ሕገ መንግሥት ታሪክ በጻፉት መጽሐፍ ላይ አስፍረዋል።

ረቂቅ ሕጎች ከተለያዩ ሚኒስትሮች የሚቀርቡ ሲሆኑ የመጨረሻው ሕግ የማውጣት ሥልጣን ግን የንጉሡ ነበር። ረቂቅ ሕጎች ግን በሁለቱም ምክር ቤቶች ውይይት ይደረግባቸዋል። የትኛውም ምክር ቤት በሚመጡ ረቂቅ ሕጎች ላይ ሐሳብ ካለው በፕሬዝዳንቱ (አፈ ጉባኤ) አማካኝነት ለንጉሡ ያቀርባል። በሁለቱ ምክር ቤቶች መካከል በረቂቅ ሕጎች ላይ አለመግባባት ካለም የሚፈታው በንጉሡ የመጨረሻ ቃል ነው።

በነገራችን ላይ የንጉሡ ሕገ መንግሥት በ1948 ዓ.ም ሲሻሻል የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት በቀጥታ በሕዝብ የሚመረጡ እንዲሆን ደንግጓል። የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባላት በመኳንንትና ሹመኞች መመረጣቸው ቀርቶ በቀጥታ በሕዝብ እንዲመረጡ ሲደረግ፤ በሕዝብ የሚመረጡት የሕግ መምሪያ ምክር ቤቱ አባላት ከ25 ዓመት በላይ መሆን፤ የራሳቸው ርስት ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲኖራቸው ይገባል። የሥራ ዘመናቸውም ለአራት ዓመታት ነው። ይህንንም ተከትሎ በአገሪቷ የመጀመሪያው ምርጫ በ1949 ዓ.ም ተደርጓል።

የሕግ መወሰኛ ምክር ቤቱ አባላት ግን አሁንም በንጉሡ ነው የሚመረጡት፤ የሚያገለግሉትም ለስድስት ዓመታት ያህል ነው።

ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ 17 ኢትዮጵያውያን እና 13 የውጭ ዜጎችን ያካተተ የሕጎችን ጥራዝ የሚያዘጋጅ ኮሚቴ አቋቋሙ። ኮሚቴው የሚሰበሰበው እና ሥራውን ይሰራ የነበረው በጊዜው ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት በአሁኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሕግ ትምህርት ቤት ውስጥ ነበር።

ከተረቀቁት የሕግ ጥራዞች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል።

የ1952 ዓ.ም ፍትሐ ብሔር፣ የ1958 ዓ.ም የፍትሐ ብሔር ሥነ ስርዓት፣ የ1949 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ፣ የ1954 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ስርዓት፣ የ1952 ዓ.ም የንግድ፣ እና የ1952 ዓ.ም የባህር ሕጎች ናቸው። ሕጎቹ የጸደቁትም ከ1949 ዓ.ም እስከ 1958 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ነበር።

በዚያ ጊዜ ከተረቀቁት ስድስት ሕግጋት አምስቱ የተለያዩ ማሻሻያዎች እየተደረገላቸው እስከ ዛሬ ተፈጻሚ ሲሆኑ አንዱ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ግን በ1997 ዓ.ም በሌላ እንደተተካ የሕግ ምሁሩ ሚኪያስ በቀለ ጥናታዊ ጽሑፍ ያመለክታል።

የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ዘመናዊ የተጻፈ ሕገ መንግሥት ከላይ የጠቃቀስናቸውን ይመስላል። ለመሆኑ ከዚህ ዘመናዊ የተጻፈ ሕገ መንግሥት በፊት የነበረው ምን ነበር የሚለውን ከሕግ ምሁሩ ሚኪያስ በቀለ ጥናታዊ ጽሑፍ ጥቂቱን እናካፍላችሁ።

ማህበረሰቡ ለዘመናት ሲተዳደር የቆየው ከአስተዋይ(አመዛዛኝ ሰው/ዳኛ) ውሳኔ በሚመነጭ ሕገ ልቦና፣ ከአይሁድ፣ ክርስትና እና እስልምና ሃይማኖቶች የሚመነጩ ሕገ ሃይማኖት፣ በሕጎች ዙሪያ ከሚሰጡ የሊቃውንት ትምህርት፣ በስምምነት ከሚገኙ እና በተስማሚዎቹ ላይ ብቻ ከሚፈጸሙ ልማዳዊ ወጎች፣ አንድ ዓይነት አሠራር ለረዥም ጊዜ ጥቅም ላይ በመዋሉ ምክንያት በተለዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ በስምምነት የሚፈጸሙ ልማዳዊ ሕግጋት፣ እና የአፈ ንጉሥ ችሎት ፍርዶች ናቸው።

ኢትዮጵያን ከ1426 ዓ.ም እስከ 1460 ዓ.ም ያስተዳደሩት አጼ ዘርዐ ያዕቆብ የተጠረዘ እና ወጥ ሕግ ለአገሪቱ እንዳበረከቱም የሚኪያስ በቀለ ጥናታዊ ጽሑፍ ያሳያል። አጼ ዘርዐ ያዕቆብ በመጀመሪያ «ፈውስ መንፈሳዊ» የሚባል በይዘቱ ሃይማኖታዊ የሆነ ባለ 68 አንቀጽ የሕግ ሰነድ በቤተክህነት ምሁራን እንዳስረቀቁ እና ለአጭር ጊዜ አገሪቷን እንዳስተዳደሩበት ይገልጻሉ።

ቀጥሎም አገሪቷን ለዘመናት ሲያስተዳድር የቆየው «ፍትሐ ነገሥት» የሚባል በይዘቱ ሃይማኖታዊና ምድራዊ ሕግጋትን ያካተተ የሕግ ሰነድ ለአገሪቷ ያስተዋወቁት አጼ ዘርዐ ያዕቆብ ናቸው። ፍትሐ ነገሥት ሃይማኖታዊ ስርዓቶችን የሚያስተዳድር 22 አንቀጽ እና 801 ንዑስ አንቀጾች፣ ምድራዊ ኩነቶችን የሚገዙ ደግሞ 29 አንቀጾች እና 1033 ንዑስ አንቀጾችን ያካተተ ነው።

በእነዚህ ልማዳዊ፣ ሃይማኖታዊና ሕገ ልቦናዊ ሕጎች ሲተዳደር የኖረው የኢትዮጵያ የነገሥታት ሥርዓት በ1923 ዓ.ም በቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ዘመናዊ የተጻፈ ሕገ መንግሥት አጸደቀ የሚለው ግን እነሆ በታሪክ ተቀምጧል።

የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት ንጉሡን ለረዥም ጊዜ ካገለገሉ መኳንንት፣ ሚንስትሮች፣ ዳኞች እና የውትድርና መኮንኖች ውስጥ በቀጥታ በንጉሡ የሚመረጡ ናቸው:: አባላቱ የመሳፍንት ዘር ባይሆኑም መንግሥትን ያገለገሉ ከሆነ ከተራ ዜጎችም ይመረጣሉ:: ይሄውም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 31 ላይ ተቀምጧል

ስፖርት እና መዝናኛ

የዝነኞች ገጽ

ሀሁ የዳንስ ቡድን

አቤል ገ/ኪዳን

በቅርቡ የኢፌዴሪ ባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር «ክብር ለጥበብ» በሚል ስያሜ ለሁለተኛ ጊዜ በተለያዩ የጥበብ ዘርፎች አስተዋጽኦ ያደረጉ ከያኒያንን ሸልሟል። ሽልማቱ ከደረሳቸው ከያኒያን መካከል ደግሞ አንዱ ሀሁ የዳንስ ቡድን ነው። ይህ የውዝዋዜ ቡድን የተመሰረተው በ2003 ዓ.ም ሲሆን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለኢትዮጵያ የውዝዋዜ ጥበብ ላቅ ያለ አስተዋጽኦ ከሚያደርጉ ቡድኖች አንዱ ሆኖ እስከ አሁን ድረስ ዘልቋል። የዛሬው የዝነኞች ገፅ አምዳችንም በዚህ የውዝዋዜ ቡድን ላይ ያተኮረ ይሆናል።

ሀሁ የተመሰረተው እዚሁ አዲስ አበባ ላይ ነው። መስራቾቹ ደግሞ ስድስት ወጣቶች ናቸው። እነሱም በድሉ ኢሳያስ፣ ዳንኤል ምስለ ወርቅ፤ ሀዋርያ አሰፋ፣ ብርሃኑ ተስፋዬ፣ ብሩክ እሱእንዳለ ይባላሉ። በወቅቱ ገና አፍላ ጎረምሳ የነበሩት እነዚህ ወጣቶች ቡድኑን ከመመስረታቸው በፊት በውዝዋዜ ፍቅር የተለከፉ ነበሩ። ሁሉም በቴሌቪዥን መስኮት በሚያዩት ፤ ሰፈር ውስጥም ሌሎች በሚያሳዩት ዳንስ የሚደነቁ እና እንደሚመለከቷቸው ዳንሰኞች የመሆን ፍላጎት ነበራቸው። ለምሳሌ ያህል ሀዋርያ አሰፋ በመጀመሪያ ደረጃ ዘፋኝ የነበረ ሲሆን የ17 ዓመት አፍላ እያለ ጓደኛው በድሉ የሂፕ ሆፕ ልምምድ ሲያደርግ አይቶ ነው ልቡ በውዝዋዜ ፍቅር የተለከፈው። ብሩክ በበኩሉ የ15 ዓመት ታዳጊ እያለ ጓደኞቹ ኮንሰርት ላይ ሲጨፍሩ አይቶ ነው ወደ ዳንስ የተሳበው። በድሉ ደግሞ አልታሰብ የተባለ አብሮ አደግ ጓደኛው በትምህርትና ሰፈር ውስጥ ሲጨፍር አይቶ ነው ዳንሰኛ መሆንን የተመኘው። ሌላኛው የቡድኑ አባል ፍቅሩ መጀመሪያ የሰርከስ አርቲስት የነበረ ሲሆን ከዚያም በ15 ዓመቱ ዳንስ ጀምሮ ነው በዚያው የቀጠለው። ኤፍሬም በ15 ዓመቱ በታዋቂው ኢትዮጵያዊ ዳንሰኛ አነሳሽነት ነበር ወደዚህ ጥበብ የገባው። በዚህ መልኩ የቡድኑ አባላት ከዳንስ ጋር የተዋወቁ ሲሆን ሚዩዚክ ሜይዴይ ውስጥም በተሰጧቸው በዳንስ ይሳተፉ ነበር።

እነሱ ሚዩዚክ ሜይዴይ በሚሰሩበት ወቅት ደግሞ በኢትዮጵያ የኪነ ጥበብ እና የቴሌቪዥን ዘርፍ አዲስ ክስተት ተፈጥሮ ነበር። ያ ክስተትም ኢትዮጵያን አይደል ነበር። ወጣቶቹም በዚህ ውድድር ላይ ለመሳተፍ ፈለጉ። ያ ፍላጎትም ሀሁ የዳንስ ቡድንን ወለደ። በ6 ወጣቶች የተመሰረተው ሀሁ በውድድሩ ላይ ተሳተፈ። በርከት ያሉ ዙሮች ያሉት ይህ ውድድር ወጣቶቹ ተሰጧቸውን እንዲያሳዩ እድል ሲከፍት በመሀል ደግሞ ተጨማሪ ሁለት አባላት ቡድኑን እንዲቀላቀሉም በር ከፈተ። የተቀላቀሉት ፍቅሩ ደምሴና ኤፍሬም ናስር ነበሩ። ዲጄ ቢንያም ሽመልስም ዘግይቶ ነበር የተቀላቀለው። በመጨረሻም ሀሁ የዳንስ ቡድን በኢትዮጵያን አይድል በዳንስ ዘርፍ ሁለተኛ በመሆንም አጠናቀቀ። በወቅቱ ቡድኑ ሁለተኛ ሆኖ ቢያጠናቅቅም የቡድኑ አባላት እድሜ እና ተሰጥኦ ግን በኢትዮጵያ ህዝብ አይን ውስጥ እንዲገቡ አደረጋቸው።

በወቅቱ ሀሁዎች በውድድሩ ሂደት አዲስ ወግ ይዘው ነበር የቀረቡት። ያ አዲስ ወግም የኢትዮጵያ ባህላዊ ውዝዋዜ ባህላዊ ሙዚቃን፣ አልባሳት ትውፊትና ታሪክን ከዘመናዊው ጋር በመቀላቀል የተፈጠረ አዲስ ስልት ነበር። ይህን ስልት በመከተል ወጣቱን ትውልድ እንደ ሂፕ ሆፕ እና ዘመናዊ ውዝዋዜ ባሉ አዳዲስ ተጽእኖዎች ተጠልፎ እንዳይሄድ ለማድረግ ሞክረዋል።

ከዚያ ውድድር በኋላ የሀሁ የከፍታና የዝና ጊዜ በይፋ ተጀመረ። በየመድረኩ እየተጋበዙ ስራቸውን እንዲያቀርቡ በሮች ተከፈቱላቸው። በዓለም የኢኮኖሚ ፎረም አመታዊ ስብሰባን ጨምሮ በትልልቅ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶች ላይ ተገኝተው በመሪዎች ፊት ስራቸውን አቅርበዋል ፤ ተቋማት በሚያዘጋጁቸው ትልልቅ መርሀ ግብሮች ላይ የመድረኩ ማድመቂያ እነሱ ነበሩ ፤ የሙዚቃ ኮንሰርቶች ላይም ከብዙ ታላላቅ ድምጻውያን ጋር ሰርተዋል። ከነዚህም መካከል ጎሳዬ ተስፋዬ ፤ አቡሽ ዘለቀ ፤ሚኪያስ ቸርነት እና ናቲ ማን ተጠቃሽ ናቸው። በሙዚቃ ቪዲዮዎች በኩልም ለአቢ ላቀው፤ ሀይሌ ሩትስ እና ሌሎች ድምጻውያን የሙዚቃ ቪዲዮዎች ላይ ውዝዋዜያቸው ተካቷል።

ሀሁዎች በውዝዋዜያቸው ውስጥ አንገብጋቢ የሚባሉ አጀንዳዎችን በማንሳት ትውልዱን ለማንቃት እና ለማስተማር ሞክረዋል። ካነሷቸው ጉዳዮች መካከል የኤች አይ ቪ ኤድስ ጉዳይ ፤ የሱሰኝነት ጉዳይ ፤ የመጤ ባህል ጉዳይ ተጠቃሽ ናቸው። አሁንም ቢሆን ዋነኛ አላማቸው ዳንስን ለማህበራዊ ጉዳዮች ማከናወኛ መጠቀም ነው።

በአሁኑ ወቅት ከቡድኑ አባላት የተወሰኑት ከአገር ውጭ ቢሆኑም ቡድኑ ግን ያለውን ሀሳብ ይዞ አሁንም ጉዞውን ቀጥሎ ስራውን እያከናወነ ይገኛል። በኪነ ጥበብ ውስጥ ብዙ ጊዜ እንደታየው የሙዚቃ ባንዶች፤ የሙዚቃ ቡድኖች እና የዳንስ ቡድኖች የመፍረስ ልማዳቸው ከፍተኛ ሲሆን ሀሁዎች ግን የተወሰነ መንገጫገጭ ቢያጋጥማቸውም አሁንም ቅርጻቸውን ሳይለቁ አብረው እየተጓዙ ነው። ከነባር አባላት መካከል በኑሮ ምክንያት ከአገር ውጭ ከሆኑት በቀር ግማሹ የቡድኑ አባል አሁንም በቡድኑ ውስጥ በንቃት እየተሳተፈ ይገኛል።

ሀሁ ኢንተርቴይንመት የተሰኘ ተቋም አቋቁመው እንቅስቃሴ እያደረጉ ያሉት እነዚህ ወጣቶች አብዛኞቹ ባለትዳር እና የቤተሰብ አስተዳዳሪ ቢሆኑም በዳንሱ ዙሪያ ብዙ የመስራት እቅድን ይዘው እየተንቀሳቀሱ ነው። ውዝዋዜን ሲጀምሩ ዋነኛ ችግር የነበረው የልምምድ ቦታ እና መሰል ችግሮች አሁን ቢቀረፉም በተቃራኒው አሁንም ለውዝወዋዜ ሙያ የሚሰጠው አመለካከት አናሳ መሆን ግን ትልቁ ተግዳሮታቸው ሆኖ እንደቀጠለ ነው። የተሰሩ ስራዎች የሚቀርቡባቸው መድረኮች አለመኖራቸውን የሚናገሩት ሀሁዎች አሁን እነሱ ተቸገረው ያረፉበትን ነገር ሌሎች እንዳይገጥማቸው የሚመለከታቸው አካላት ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ይወተውታሉ።

ከውትወታም ባለፈ በየጊዜው በርካታ ታዳጊዎችን በውዝዋዜው በኩል እያሰለጠኑ ይገኛሉ። እነሱ ካሰለጠኗቸው ወጣቶች መካከል ቴአትር ቤት የተቀላቀሉ ፤ እንዲሁም የራሳቸውን የዳንስ ቡድን መስርተው እየተንቀሳቀሱ ያሉ ይገኙበታል። የዳንስ አሰልጣኝ የሆኑም አሉበት። ወደፊት የዳንስ ትምህርት ቤት ለመክፈትም ይመኛሉ። ለዚህም ከሚመለከተው የመንግስት አካል ጋር በመሆን ስርዓተ ትምህርት ለመቅረጽ ጥረት እያደረጉ ነው።

ከስራ ውጭ የሀሁ አባላት እስከ ቤተሰብ የዘለቀ ወዳጅነት ያላቸው ሲሆን በእረፍት ጊዜያቸውም አብረው በመጫወት እና መንፈሳዊ ተግባራትን በመፈጸም የሚውሉበት አጋጣሚ ብዙ ነው።

ፍቅረማርቆስ ደስታ

ፍቅረማርቆስ ደስታ ይባላል። በ1955 በጎጃም ክፍለ ሀገር ነው የተወለደው። በ1980ዎቹ መጀመሪያ ላይ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኬሚስትሪ ዲፓርትመንት በዲግሪ ተመረቀ። በተመሳሳይ ጊዜ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር ሆኖ በደቡብ ኦሞ ዞን፣ ጂንካ ከተማ ተመደበ። እዚያ መኖር ሲጀምርም በዞኑ ባሉት አስራ ስድስት ብሔረሰቦች ቋንቋ፣ አለባበስ፣ አመጋገብ፣ ጌጣ ጌጥ፣ የኢኮኖሚ ስምሪት፣ ባህላዊ ዳኝነት፣ ማህበራዊ ሕይወት፣ ሙዚቃ፣ ዳንኪራ፣ አፈ-ታሪክ፣ ስነ-ቃል ወዘተ ተማረከ።

ፍቅረማርቆስ ያየውን ነገር በማድነቅ ብቻ አልታቀበም። ከመምህርነት ሙያው ጎን ለጎን ያየውንና የሰማውን ነገር በጥልቀት አጥንቶ ለመከተብ ወሰነ። በዚህም መሠረት ከብሄረሰቦቹ መካከል እርሱ ላለበት አካባቢ ቀረብ የሚለውን የሀመርን ሕዝብ ባህል፣ ቋንቋ፣ ታሪክ፣ ኪነ-ጥበብ እና ትውፊት በማጥናት ያገኘውን ውጤት እንደ ግብአት ተጠቅሞ ኢትኖግራፊያዊ የፈጠራ ጽሑፎችን መጻፍ ጀመረ። በ1987 የመጀመሪያ ድርሰቱ የሆነውን "ከቡስካ በስተጀርባ"ን ለህትመት አበቃ።

ፍቅረማርቆስ መጽሐፉን ለህትመት ሲያበቃ ይዞት የተነሳው ጭብጥ ስለፍቅር እና ወንጀል መጻፍ በለመዱት ደራሲዎች እና በዚህ ዐውድ የተጻፉትን ድርሰቶች ማንበብ በለመደው ተደራሲ ዘንድ አጓጊ እና አነጋጋሪ መሆን አልቻለም ነበር። በአንትሮፖሎጂ እና ታሪክ ጥናት ዘርፍ የተሰማሩ ምሁራን ግን ስራውን በጣም ነው ያደነቁለት። አንዳንዶቹም በዘመኑ ጋዜጦች እና መጽሔቶች ላይ የተለያዩ ግምገማዎችን ጽፈውበታል። ከዓመት በኋላ ደግሞ መጽሐፉ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስር ባለው የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም "ፍኩይ" የተሰኘ ሽልማት ተሸልሟል።

በዚህ የተነቃቃው ደራሲ ፍቅረማርቆስ በ1990 በብዙዎች ዘንድ የሚወደደውንና የእርሱ ምርጥ ስራ ለመሆን የበቃውን "ኢቫንጋዲ"ን ለአንባቢያን አበረከተ። በተከታዮቹ ዓመታትም " የዘርሲዎች ፍቅር"፣ "አቻሜ" እና "የንስር ዐይን" የተሰኙትን መጻሕፍት አሳተመ። በ1995 ገደማ አምስቱንም መጻሕፍት በአንድ ላይ አጠቃልሎ ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሞ ሲያበቃ መጽሐፉን "Land of the Yellow Bull" በሚል ርእስ ለህትመት አበቃ

ደራሲ ፍቅረ ማርቆስ ደስታ በመጽሐፎቹ የሀመርን ሕዝብ በማስተዋወቅ ብቻ አልቆመም። በብሔረሰቡ ደንብ መሠረት የሀመሮች አካል ሆኖ ከእነርሱ ጋር ኖሯል። ሀመሮች ደራሲው በብዕሩ የዋለላቸውን ውለታ በደንብ በመገንዘባቸው እንደ አንጋፋ ልጃቸው ይመለከቱታል። ይሁን እንጂ በ2004 "እሄዳለሁ" ብሎ ሳያስታውቃቸው ወደ አሜሪካ በመሻገሩ በጣም ተናደውበት ነበር።

ፍቅረ ማርቆስ በአሜሪካ ለአስር ዓመት ያህል ከቆየ በኋላ አምና ወደ አገሩ ተመልሷል። ታዲያ ደራሲው ወደ ሀመሮች ዘንድ ሲደርስ በዝምታ አልታለፈም። "በባህላችን መሠረት ጠፍቶ የመጣ ሰው ወደ ሕዝቡ የሚቀላቀለው ከተገረፈ በኋላ ነው" ሲሉት ለመገረፍ አላቅማማም። ቅጣቱን ከተቀበለ በኋላም ከሚወዳቸው የሀመር ብሔረሰብ አባላት ጋር ተቀላቅሏል።

ሀመር የሚባለው ኩሻዊ ቋንቋ ተናጋሪ ብሔረሰብ በኢትዮጵያ ምድር ለረጅም ጊዜ ነው የኖረው። በቀድሞ ዘመናት ስለዚህ ሕዝብ ባህል፣ ታሪክ እና ትውፊት የነበረን እውቀት በጣም ውስን ነው። የሀመር ማንነት ወለል ብሎ የታየን ደራሲ ፍቅረ ማርቆስ ደስታ ባደረገው የብዕር ተጋድሎ ነው። ደራሲው ብዙ የለፋበት ብሔረሰቡን የማስተዋወቅ ስራ ውጤት ማምጣቱንም በራሱ ዓይን ለማየት ችሏል።

ለምሳሌ በድሮ ዘመን የ"ኢቫንጋዲ"ን ምንነት የሚያውቅ ሰው እጅግ በጣም ጥቂት ነው። ባለፉት ሃያ ዓመታት ግን "ኢቫንጋዲ" በብዙዎች ዘንድ የሚታወቅ ጽንሰ ሐሳብ ለመሆን ከመብቃቱ ባሻገር ለብዙ የፈጠራ ስራዎች መነሻ ሲሆን አይተናል። በዚህ ረገድ ጎሳዬ ተስፋዬ የተጫወተው "ኢቫንጋዲ" የተሰኘው ተወዳጅ ዘፈን እንደ አብነት ሆኖ ሊነሳ ይችላል።

ሥነ ምግባርና አስፈላጊነቱ

ጽጌረዳ ጫንያለው

ልጆች እንደምን አላችሁ፤ ዕረፍት ተጀመረ አይደል? መቼም ደስተኛ ሆናችሁ እያሳለፋችሁ እንደሆነ አምናለሁ። ይህ ክረምት ካለፉት ክረምቶች ሁሉ ከባድ እንደሆነባችሁ አስባለሁ። ይሁንና እናንተ ጎበዞች ስለሆናችሁ ትቋቋሙታላችሁ። አንድ ነገር ግን ልንገራችሁ፤ በብርድ እንዳትታመሙ ወፍራም ልብሶችን መልበስን መዘንጋት የለባችሁም። በዚያ ላይ ለመጫወት ከባድ ዝናብ እየጣለ እንዳትወጡ። ጎርፍ ሊኖር ስለሚችል በእንቅስቃሴያችሁ ልክ መጠንቀቅ አለባችሁ እሺ? ጎበዞች! ዛሬ ይገርላችሁ የቀረብኩት ስለ ሥነ ምግባር ምንነትና አይነት ነው።

ቤተሰብና የአካባቢውን ማህበረሰብ አክባሪ እንድትሆኑ ሥነ ምግባር ያለው ልጅ መሆን እንዳለባችሁ ታውቃላችሁ አይደል? ግድ ነው። ለመሆኑ ሥነ ምግባር ማለት ምን ማለት ይሆን? እናንተ ደግሞ በስነ ዜጋና ሥነ ምግባር ትምህርት ይህንን እንደተረዳችሁ አምናለሁ። ይሁንና ላላወቃችሁ ወይም ደግሞ ላላነበባችሁ ዛሬ ከተለያዩ መረጃ ምንጮች ያሰባሰብኩትን አስነብባችኋለሁ። የምታውቁ ካላችሁም ላላወቁ እንድታሳውቁበት ይጠቅማችኋልና በደንብ አንብቡት።

ሥነ ምግባር በሰው ልጅ ሥልጣኔ ምስረታ ውስጥ ቁልፍ ጽንሰ ሀሳብ ነው። በሌላ በኩል በዜጎች መካከል ማህበራዊ ሰላምን እና አንጻራዊ ስምምነትን ለማረጋገጥ የትኛውን ማክበር እንዳለበት የሚያስቀምጥ ሕግም ነው። ሌላው ሥነ ምግባር የሰው ልጅ ታሪክ ወሳኝ አካል ነው። ምክንያቱም ማንነቱ የሚለካው በነበረው የሥነ ምግባር ልኬት ነው። የእያንዳንዱ ዕድሜ ሥነ ምግባራዊነት በአብዛኛው ማህበራዊ ኃይሎች የሚገናኙበትን መንገድ ይወስናልም።

ልጆች የሥነ ምግባር ሌላው ባህሪ የአንድ ማህበረሰብ ታሪካዊ እና ባህላዊ ወግ አካል መሆኑ ነው። መልካምን እና ክፉን ለመለየት ያገለግላል። ነፃ ፈቃድ እና ሕሊናን በአኗኗራችን ውስጥ ለመዳኘት፤ ለመረጋጋት እና ለማኅበራዊ ስምምነት አስተዋፅኦ የሚያደርጉትን ነገሮች ለመለየት እንድንችል ያደርገናልም። ማለትም እሴቶች ብቅ እንዲሉ እና እንዲኖሩን ይፈቅዳል።

ሥነ ምግባር ከሃይማኖት ጋር በቅርበት የተሳሰረ ጉዳይ እንደሆነ ምሁራን ይናገራሉ። ነገር ግን በመንግሥት እና በሃይማኖት መካከል መለያየት ሲፈጠር ከሲቪክ እና ከማህበራዊ ሕይወት ጋር ሊያዝ ችሏል። ሆኖም ይህም ተደርጎ ሃይማኖታዊ የሥነ ምግባር ሕጎች አልቀሩም። ከዘመናዊነት በኋላ በከፍተኛ ሁኔታ መለወጣቸው ቢኖርም። ይህ ደግሞ የሰው ልጅ ፅንሰ ሀሳቦቹን እና የሥነ ምግባር ደንቦቹን እንደገና እንዲገነዘባቸው አስገድዶታል። ለዚህም ነው ሥነ ምግባር ወይም ሞራል የምንለው ዛሬ በሳይንስ፣ በሙያዎች ልምምድ እና በሌሎች መስኮች የተሳትፎ ኮታ አለው የሚባለው። ሃይማኖታዊ ተቋማት ማስተማራቸውን ባያቋርጡም የሰው ልጅ በዓለማዊ ፣ ማለትም ከሃይማኖታዊ አስተምሮ ውጭ በሆነ የሥነ ምግባር ዳኝነት መተዳደር የጀመረውም በዚህ ምክንያት እንደሆነ ይነገራል።

ልጆች ለመሆኑ የሥነ ምግባር አይነቶች ምን ምን እንደሆኑ ታውቃላችሁ? የተወሰኑትን እስኪ እንንገራችሁ። የመጀመሪያው ሃይማኖታዊ ሥነ ምግባር የምንለው አይነት ነው። ይህ የሥነ ምግባር አይነት በተወሰኑ ምስጢራዊ ወይም ሃይማኖታዊ ወጎች የሚወሰን እና በእምነቱ ወይም በትምህርቱ ትዕዛዛት የሚገዛ ነው። በተለይም በመሠረታዊ ዘርፎች ጉዳይ የበለጠ ግትር ወይም የማይለዋወጥ ሥነ -ምግባር ሊሆን ይችላል።

ሌላውና ሁለተኛው የሥነ ምግባር አይነት ዓለማዊ ሥነ ምግባር የሚባለው ሲሆን፤ ምንም እንኳን ብዙዎቹ እሴቶቹ በሃይማኖታዊው ዘመን በጥብቅ ከተጠቆሙት ከባህላዊ ወጎች ጋር ቢገጣጠሙም የራሱ የሆነ መለያ ያለው ነው። ይህም በምስጢራዊ ወይም በሃይማኖታዊ ወግ የማይወሰን መሆኑ ነው።

በሦስተኛ ደረጃ የምናነሳው የሥነ ምግባር አይነት መሠረታዊ ሥነ ምግባር የሚባለውን ነው። ይህ አይነቱ ሥነ ምግባር ሁለንተናዊ ለመሆን የሚፈልግ ነው። ማለትም በሰው ልጅ ሕልውና ውስጥ በጣም መሠረታዊ አካላትን የመፍረድ አዝማሚያ አለው። ለምሳሌ፡- ሰብዓዊ መብቶች (ሰብዓዊ መብቶች) በዚህ ዓይነት ሥነ ምግባር ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

አራተኛው አይነት ደግሞ ማህበራዊ ሥነ ምግባር ተብሎ የሚጠራው ነው። በዚህ ስም የኅብረተሰቡን የሞራል ትዕዛዛት ማለትም ባህላዊ እና ውርስ ወይም በአንድ ቡድን ውስጥ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሚገዛውን የሚይዝ ነው። አንድ ግለሰብ በውስጣዊ መድረኩ ውስጥ ሊኖረው ከሚችለውም ይለያል። ምክንያቱም አዛዥም ናዛዥም ማህበረሰቡ ብቻ የሆነበት ነው።

የመጨረሻውና በአምስተኛ ደረጃ የምናነሳው የሥነ ምግባር አይነት ደግሞ ግለሰባዊ ሥነ ምግባር የምንለው ነው። ይህ እያንዳንዱ ሰው ወደ ጥሩ እና መጥፎ ጽንሰ -ሐሳቦች የሚወስደው ለግል፣ ለነጠላ እና ለግል አቀራረብ የተሰጠ ስም ነው። በእውነቱና ተጨባጭነቱ ላይ ለመገምገም በራሱ አቅም አለው። ከፊሉ የሚወሰነው በጋራ ወይም በማህበራዊ ሥነ ምግባራዊነት የሚደነግገውን አልቀበልም ማለትና የራሱን ማስቀመጥ የሚችልበትም ነው።

ልጆች ከእነዚህ ባህሪያቱ አንጻር ደግሞ ሥነ ምግባርን በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል። መልካም ሥነ ምግባር ያለውና ሥነ ምግባር የጎደለው በሚል። ሥነ ምግባር የጎደለው ስንል ከሥነ-ምግባር የተለየ እይታ ጋር የሚቃረን ነው። ሕጎቻቸውን የሚጥስ፣ ራዕዮቻቸውን የሚቃረን እና ትዕዛዞችን የማያከብርም ማለታችን ነው። ለምሳሌ፡- በአንዳንድ የእስልምና እና የአይሁድ ባህሎች ውስጥ ሴቶች ፀጉራቸውን በነፃነት ማሳየታቸው ሥነ ምግባር የጎደለው ነው ተብሎ ይታሰባል። ስለሆነም በሻርፕ የመሸፈን ግዴታ አለባቸው።

ሥነ ምግባር ያለው ማለት ደግሞ ለሞራል ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጥ፤ መልካሙን ብቻ እያየ የሚፈጽም፤ ክፉውን ከደጉ የሚለይ፤ ለሰው ልጅ ሁሉ የሚሰራና ግለኛ ያልሆነ ፤ ለመልካም ነገር ሲባል እንደ ሁኔታው እና እንደ አውዱ ተለዋውጦ የሚሰራ፤ ምክንያታዊ የሆነ ሰው ማለታችን ነው። ልጆች እናንተም መሆን ያለባችሁ ይህንን አይነት ሰው ነው እሺ? ብዙ ሀሳቦችን በዚህ ጽሁፍ እንደጨበጣችሁ አምናለሁ። እናም ተጨማሪ ነገርም አንብባችሁ እውቀታችሁን አዳብሩ በማለት ለዛሬ አበቃሁ። በሚቀጥለው ሳምንት በሌላ ጉዳይ እስክንገናኝ ድረስ ቸር ሰንብቱ !!

ስፖርት

ለሁለት ወርቆች የታጨው የወቅቱ የረጅም ርቀት ተወርዋሪ ኮከብ

ብርሃን ፈይሳ

በዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና የሜዳሊያ ሰንጠረዥ ታሪክ ኢትዮጵያ 85 ሜዳሊያዎችን በማስመዝገብ ሰባተኛ ደረጃ ላይ ትቀመጣለች። ከእነዚህ ሜዳሊያዎች መካከል 36 የሚሆኑት የተገኙት ኢትዮጵያ በምትታወቅበት የረጅም ርቀት ሩጫዎች ነው። ከእነዚህ ርቀቶች 10ሺ ሜትር በርካታ ሜዳሊያዎች የተመዘገቡበት ሲሆን፤ 10 የወርቅ፣ 5 የብር እና 4 የነሃስ በጥቅሉ 19 ሜዳሊያዎች ተገኝተውበታል። በዚህ ርቀት ስኬት የጀግናውን አትሌት ቀነኒሳ በቀለን ያህል የገዘፈ ታሪክ ያለው ኢትዮጵያዊ አትሌትም የለም።

ቀነኒሳ በአራት የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ተሳትፎው (ፓሪስ፣ ሄልሲንኪ፣ ኦሳካ እና በርሊን) ቻምፒዮናዎች በ10ሺ ሜትር 4የወርቅ ሜዳሊያዎችን ሲያጠልቅ፣ በ5ሺ ሜትር ደግሞ አንድ የወርቅ እና የነሃስ ሜዳሊያዎችን አግኝቷል። በአንድ ውድድር በሁለት ርቀቶች የወርቅ ሜዳሊያዎችን የግሉ በማድረግም ብቃቱን ያስመሰከረ አትሌት ነው። ይኸውም እአአ በ2009 የበርሊን ዓለም ቻምፒዮና በቀናት ልዩነት በሁለቱም ርቀቶች የወርቅ ሜዳሊያዎችን በማጥለቅ አስደማሚ ብቃቱን ያሳየበት ሆኖ ይታወሳል። ይህም ስኬት በአትሌቲክስ የታሪክ ማህደሮች ስሙን በደማቅ እንዲፃፍ አድርጓል።

ከቀነኒሳ ወርቃማ የውድድር ዘመን በኋላ ባሉት ቻምፒዮናዎች ግን ኢትዮጵያ በሁለቱም ርቀቶች ያገኘቻቸው ሜዳሊያዎች ቁጥር ቀንሷል። እንደ ቀነኒሳ ሁሉ በሁለቱንም ርቀቶች የሚደፍር አትሌት ባለመገኘቱ የተነሳም በእንግሊዛዊው አትሌት ሞሃመድ ፋራህ የበላይነት ተይዞ ቆይቷል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህም በወጣቶቹ አትሌቶች ኢትዮጵያ ዳግም ወደ ውጤት የመመለስ ተስፋ እያሳየች ትገኛለች። ከተጀመረ ዛሬ ሶስተኛ ቀኑን በያዘው 18ኛው የኦሪጎን ዓለም ቻምፒዮናም ምናልባትም ሁለቱን ርቀቶች በማሸነፍ የጀግናውን አትሌት ቀነኒሳ በቀለ ታሪክ የሚጋራ አትሌት እንደሚፈጠር በርካቶች ተስፋ አላቸው።

ወጣቱ ኮከብ አትሌት ሰለሞን ባረጋ ዛሬ በ10ሺ ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ እንደሚያጠልቅ ይጠበቃል፣

ታሪክ ለመስራት በኦሪጎን የተገኘው ሰለሞን ዛሬ ምሽት በ10ሺ ሜትር ከቀናት በኋላ ደግሞ በ5ሺ ሜትር ይሮጣል። አገሩን ከመወከል ባለፈም የቀነኒሳን ታሪክ መድገም የምንጊዜም ምኞትና ፍላጎቱ እንደሆነ የሚናገረው ሰለሞን፣ ታሪክ ሰሪ ለመሆን በዚህ ውድድር ላይ በቂ ዝግጅት አድርጓል። ሰለሞን ወደ ኦሪገን ከማቅናቱ በፊት ከአዲስ ዘመን ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ «እኔ ባላሳካውም ጓደኞቼ ያሳኩታል፤ እንደ ቡድንም ጥሩ ውጤት እናመጣለን» ሲል በርቀቶቹ የሚጠበቁት ድሎች ከእሱ እጅ ቢወጡም ከኢትዮጵያ እንደማያመልጡ ይናገራል።

በስፖርት ቤተሰቡ ዘንድ የሁለት የወርቅ ሜዳሊያዎች ባለቤት ይሆናል የሚል ተስፋ የተጣለበት ይህ ድንቅ ወጣት አትሌት፤ ባለፈው የዶሃ የዓለም ቻምፒዮና ሙከታር እድሪስን ተከትሎ በመግባት በ5ሺ ሜትር የብር ሜዳሊያ ማጥለቁ የሚታወስ ነው። ይኸውም አትሌቱ በርቀቱ ያለውን ብቃትና ውጤታማነት ያሳየ ሆኗል። በኦሪገኑ ቻምፒዮና ላይም ካለው አስደናቂ ወቅታዊ አቋም አንጻር በሁለቱም ርቀቶች ወርቆችን ያጠልቃል ተብሎ ይጠበቃል።

የ10ሺ ሜትርን ድል ከሁለት ኦሊምፒኮች በኋላ ቶኪዮ ላይ ማሳካት የቻለው ይህ ወጣት የረጅም ርቀት ተወርዋሪ ኮከብ አስደናቂ አጨራረስ ብቃቱና የማይደክሙ እግሮቹ ዛሬ ተዓምራቸውን ለዓለም ማሳየት እንደሚጀምሩ ይጠበቃል። ሰለሞን በዘንድሮ ዓመት በቤልግሬድ የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና በ3ሺ ሜትር አሸንፎ የወርቅ ሜዳሊያውን ያጠለቀበት ሂደትም ለዚህ ማረጋገጫ ነው። ባለፈው ወር በዳይመንድ ሊግ ውድድር በፓሪስ 5ሺ ሜትርን በከባድ የአየር ንብረት ተፎካካሪዎቹ እስከማቋረጥ ሲደርሱ እሱ ያሸነፈበት ውድድርም የዛሬው የ10ሺ ሜትር ወርቅ የግሉ እንደሚሆን ፍንጭ የሰጠ ነው። «ለዚህ ቻምፒዮና ጥሩ ዝግጅት ስናደርግ ቆይተናል» የሚለው ሰለሞን፤ በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በኩል የብሄራዊ ቡድን ጥሪ እስከሚደረግ ጊዜው ቢዘገይም ይህንን ውድድር ያማከለ ዝግጅት በግሉ ሲያደርግ መቆየቱን ተናግሯል። ከጥሪው በኋላም ከቡድኑ አባላት ጋር መልካም የሚባል ዝግጅት አከናውኗል። ዓመቱ በርካታ የግልና የአገር ውድድሮች የነበሩበት ሲሆን፤ የሄንግሎው የሰዓት ማሚያም በመዘግየቱ ከውድድሮች ጋር እጅግ የተቀራረበ ጊዜ ላይ በመከናወኑ አትሌቶች ላይ ጫና ነበረው። ከሄንግሎው ማጣሪያ በኋላ ግን ከውድድሮች በመታቀብ እሱና የቡድን አጋሮቹ ወደ ዝግጅት መግባታቸውን ያስረዳል።

በዚህ ዓመት በ10ሺ ሜትር በርካታ ውድድሮች ያልተደረጉበት እንደመሆኑ ተፎካካሪዎቻቸው ያሉበትን ሁኔታ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው። ከኬንያ በቀር ሌሎች ቡድኖች የሰዓት ማሚያ ሲያደርጉም ባለማሳወቃቸው ምክንያት የትኛው አትሌት ምን አይነት ብቃት ላይ እንደሚገኝ ለመገመት አስቸጋሪ ነው። እንደ ኢትዮጵያ ግን መልካም አቋም ላይ በሚገኙ አትሌቶች የተገነባ ቡድን ወደ ኦሪገን እንደተጓዘ ይታመናል። ከዚህ ቀደም ሰለሞንና ሌሎች ወጣት አትሌቶች ከልምድ አንጻር ያለባቸው ክፍተት ካለፈው ጊዜ ትምህርት በማግኘት የተሻለ ውጤት ለማምጣት በሚያስችል ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ብርቅየው አትሌት አስተያየቱን ሰጥቷል።